# የእግዚአብሔር ዓላማ ለእስማኤል

ጥቅምት 1998 ዓ.ም

ታተመ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Right Reserved

## ማ ው ጫ

ገጽ


መግቢያ

I. ለወንጌል አገልግሎት ራስን ማዘጋጀት የነህምያ ፅናት ምስጢር ........ 1

ሀ. በእግዚአብሔር ታመነ ........ 7

ለ. የነህምያ ፀሎት ........ 9

ሐ. እግዚ/ርን ማሰቡ ........ 13

መ. ዋጋ ለመክፈል የተዘጋጀ ሰው መሆኑ ........ 17

II. እስልምና

የእስልምና ሃይማኖት መልእክተኛ የነቢዮ መሀመድ ታሪክ ........ 24

1. የኢማን /እምነት/ መሰረቶች ........ 29

2. በእስልምና ስርያሉ የእምነት ክፍሎች ........ 30

3. ቁርዓን ........ 34

4. የእስልምና ግንዛቤ

ሀ. ስለ ሰው ........ 35

ለ. ስለኃጢአት ........ 38

5. በእስልምና መንግስተ ሰማያት ለመግባት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች እና ስለመጨረሻው ዘመን

ሀ. ስለድነት ........ 41

ለ. ምፅአቱን ወይም ስለመጨረሻው ቀን ያላቸው አመለካከት ........ 44

III. የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በቁርዓንና በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ ........ 50

1. ነቢያትና ሐዋሪያት ኢየሱስ ማን ነው ለሚለው ጥያቄ መልስ ሰጥተዋል ........ 55

2. የክርስቶስ ስቅለት

ሀ. በቁርዓን ..................................................... 61

ለ. በመጽሐፍ ቅዱስ ..................................... 63

3. በቁርዓን ለኢየሱስ የተሰጠው ስያሜ ..................... 73

4. የኢየሱስ መለኮትነት በቁርዓን ................................ 84

5. ጌታ ኢየሱስ ለምንድን ነው ሥጋ ለብሶ ወደዚህ ዓለም የመጣው ..................................................... 85

IV. ለሙስሊሞች እንዴት ነው መመስከር ያለብን ? 88

ሀ. በእነርሱ መሀል ስታገለግል ........................ 94

ለ. አገልግሎትህ በፍቅር የተቀመመ መሆን አለበት ......................................................... 96

V. ሥላሴ በቁርዓን

ሀ. ቁርዓን ስለ ሥላሴ ትምህርት ምን ይላል ? .......... 100

ለ. ሥላሴ በመጽሐፍ ቅዱስ ..................................... 114

VI. ወንጌል እውነት መሆኑን እንዴት አውቃለሁ ............... 122

VII. መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ተበርዟል ? .......................... 131

ስለመጽሐፍ ቅዱስ መበረዝና አለመበረዝ

ቁርዓን ምን ይላል ? ................................................. 135

ሙስሊሞች እንዲህ ያምናሉ ? ........................................ 147

VIII. ምስክርነትህን በጥያቄ ጀምር ........................................ 148

# መግቢያ

ከዚያም አሥራ አንዱ በማዕዱ ላይ ሳሉ ተገለጠላቸው ከተነሣ በኋላ ያዩት ሰዎች የነገሩቸውን ስላለማመናቸው የልባቸውን ድንዳኔ ነቀፈ:: እንዲህም አላቸው ወደ አለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ያመነ የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል::"ማር. 16:14-15

የዚህ መጽሐፍ አብይ ርእስ ለእስማኤል የእግዚአብሔር ዓላማ በሚል ተዘጋጅቶአል:: የመጽሐፉ ትኩረት ሙስልሞችን በወንጌል የምንደርስበት መንገድ ለማሳየት ነው::

እኛ የወንጌል አማኞች መጽሐፍ ቅዱሳችንን ማንበብና እንደ ቃሉ መኖር ከእኛ ይጠበቃል:: "ሕይወት የሚሰጡትን ትዕዛዛት ቢከተል ክፉ ነገርንም ባያደርግ በእርግጥ እርሱ በሕይወት ይኖራል:: አይሞትምም" ሕዝ. 33፥15

እንደዚሁም ሌሎች ወገኖችን በወንጌል የምንደርስበት መንገድ ማወቅ ተገቢ ነው:: ሙስሊም ጐረቤቴን ስለ ጌታ እንዴት አድርጌ ነው የምነግረው? ከየት ልጀምርለት የሚል ጥያቄ ብዙዎች ይጠይቃሉ:: ይህን ጥያቄና ሌሎችንም በሚመልስ መልኩ መጽሐፉ ተዘጋጅቶአል::

በውስጡ የቁርዓን ጥቅሶች የያዘ በመሆኑ ለብዙ ክርስቲያኖች እንግዳ ሊሆንባቸው ይችላል:: ሆኖም ቁርዓንን የማንበብ አጋጣሚ ይፈጥርላቸኋል:: ቁርዓን ስለ ክርስቶስ ምን ይላል? ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እና ስለ መጽሐፉ ሰዎች ወይም ስለ ክርስያኖች ምን ይላል መልሱን ከመጽሐፉ ያገኛሉ:: ከሙስሊሞች ጋር ስለ ወንጌል በፍቅር የምንወያይበት አቅጣጫ ያሳያናል::

ይህ መጽሐፍ ለየት ባለ መንገድ የተዘጋጀና በአካባቢያችን ያሉ ወንጌል ያልደረሳቸው ሙስሊም ወገኖቻችን እንዴት በወንጌል መድረስ እንዳለብን በር ከፋች መጽሐፍ ነው።

እግዚአብሔርም ልጁ ምርር ብሎ ሲያለቅስ ሰማ የእግዚአብሔር መላአክ ከሰማይ አጋርን «አጋር ሆይ የምትጨነቂበት ነገር ምንድን ነው ? እግዚአብሔር የልጁን ለቅሶ ሰምቶአልና አይዞሽ አትፍሪ ተነሽ ሂጂና ልጁን አንስተሽ አባቢይው የእርሱንም ዘር አበዛለሁ ታላቅ ሕዝብ አደርገዋለሁ » አላት በዚህም ጊዜ እግዚአብሔር አይኖቿን ከፈተላትና አንድ የውሃ ጉድጓድ አየች ሄዳም በአቅማዳው ውሃ ሞላች ለልጇም አጠጣችው ። ልጁም እያደገ በሄደበት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረ በፋራንም በረሃ ኖረ ቀስት በመወርወር የታወቀ አዳኝ ሆነ ዘፍ. 21:17-20

ወደ አንተ ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትኾን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ። እውነቱ መጥቶልሃል ከተጠራጣሪዎቹም አትኾን ። ሱራ 10:94

ከጌታህም መጽሐፍ ወደ አንተ የወረደውን አንብብ ። ለቃላቶቹ ለዋጭ የላቸውም ከእርሱ በቀር መጠጊያ አታገኝም ። ሱራ 18:27

## I. ለወንጌል አገልግሎት ራስን ማዘጋጀት

የተሰጠን የፍቅር ትዕዛዝ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ» ማር. 16፥15 "አንተ ልጄ ሰለሞን ሆይ እግዚአብሔር ልብን ሁሉ ይመረምራልና የነፍስንም ሃሳብ ሁሉ ያውቃልና የአባትህን አምላክ እወቅ በፍፁም ልብና በነፍስህም ፈቃድ አምልከው ብትፈልገው ታገኘዋለህ ብትተወው ግን ለዘላለም ይጥልሃል። ጠንክር አይዞህ አድርገውም አምላኬ አምላክህ ከአንተ ጋር ነውና አትፍራ አትደንግጥም ለእግዚአብሔርም ቤት አገልግሎት የሚሆነው ስራ ሁሉ እስኪፈፀም ድረስ እርሱ አይተውህም አይጥልህምም"።

1ዜና 28፥9:20

የተሰጠንን አደራ እንዳንወጣ ትልቁ እንቅፋት ፍርሃት ነው።ፍርሃት ከእግዚአብሔር ሀሳብ ወደ ኋላ የሚያስቀር የሰይጣን መሣሪያ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ፈራሁ ያለው አዳም ነው። የተሰጠው ትዕዛዝ መተላለፉን ስለሚያውቅ ወዴት ነህ? ሲለው ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ውስጥ ገብቶ የአንተን ድምፅ ሰማሁ ራቁቴን ስለሆንሁ አንተን በመፍራት ተደበቅሁ አለ።

ፍርሀት ወደ ሰው ህይወት የሚመጣበት መንገድ የተለያየ ነው። በድምፅ በአይን አስፈሪ የሆነ ነገር በማየት በሀሳብ እና በሌሎችም ምክንያቶች ሰዎች ፈራሁ ይላሉ። አዳም በምሽት የሚሰማው የእግዚአብሔር ድምፅ ለይቶ ያውቃል። የማያውቀው ድምፅ ሲሰማ አስፈራው ምክንያቱም ድምፁን የሚሰማበት ፀጋው ስለተለየውና የሰራው ስራ ትክክል እንዳይደለ ስለ ተረዳ ነው። ልጆች የአባታቸውን ድምፅ ሲሰሙ ሮጠው ይጠመጠሙበታል ጥፋት በሚያጠፉበት ጊዜ ግን የአባታቸውን ድምፅ ሰምተው ጓሮ ይደበቃሉ።

ጌታ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የወንጌል አደራ ከመስጠቱ በፊት በውስጣቸው ያለውን ፍርሀት ማውጣት ነበረበት ሉቃ. 12፥4-9፣13፥21-32 «ለእናንተ ለወዳጆች እላችኋለሁ ሥጋን ከመግደል በቀር ሌላ ምንም ማድረግ የማይችሉትን አትፍሩ ነገር ግን ማንን መፍራት እንዳለባችሁ እነግራችኋለሁ፤ይኸውም ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም ለመጣል ሥልጣን ያለውን እግዚአብሔርን ነው»:: አዎን እርሱን ብቻ ፍሩ:: ሊሆን ያለውን ሁሉ የሚያውቅ ጌታ ለአገልግሎት የሚያዘጋጅ ትምህርት አስተማራቸው::

አምስት ድንቢጦች በአሥር ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱ አንድዋ እንኳ በእግዚአብሔር ፊት የተረሳች አይደለችም:: የእናንተም የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳን የተቆጠረ ነው:: ስለዚህ አትፍሩ እናንተ እኮ ከብዙ ድንቢጦች ትበልጣላችሁ:: ይህ ማለት ከፀጉራችሁ በታች ያለው መላ አካላችሁ ይጠነቀቅለታል ማለቱ ነው ::

ኢየሱስም እንዲህ አለ «ሳያፍር በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ እኔም ደግሞ በእግዚአብሔርና በመላእክት ፊት እመሰክርለታለሁ በሰው ፊት የሚክደኝ እኔም ደግሞ በእግዚአብሔርና በመላእክት ፊት እክደዋለሁ»:: ስለ ክርስቶስ ላልዳኑት ሰዎች አለመመስከር ክህደት ነው::

የሚወደን የምንወደው ትምክህታችን የምንተማመንበት አምላካችን ለመጪውም ዘመን ተስፋችን የሰጠን ተልከ በመዘንጋታችን አላውቃችሁም እንዳይለን ስለ እርሱ እንመስክር::

"ጌታ በመቀጠል እንዲህ አለ የሰው ህይወት በሀብት ብዛት አይደለም ስለዚህ ከመጐምዠት ከስግብግብነት ተጠበቁ ተጠንቀቁም" 1ጢሞ. 6፥17-19 የዚህ ዓለም ሀብታሞች እንዳይታበዩ ወይም ተስፋቸውን በሚጠፋ ሀብት ላይ እንዳያደርጉ እዘዛቸው:: እንዲሁም ተስፋቸው እኛን ደስ እንዲለን ሁሉን ነገር አትረፍርፎ በሚሰጠን

በእግዚአብሔር ላይ እንዲሆን አዘዛቸው:: ደግሞም መልካም ሥራ እንዲሰሩ በመልካም ሥራ ሀብታሞች እንዲሆኑ ለመለገስና ያላቸውን ለማካፈል ዝግጁዎች እንዲሆኑ አዘዛቸው:: በዚህ ዓይነት እውነተኛውን ሕይወት ለማግኘት መሠረቱ ጽኑ የሆነውን ሀብት ከሚመጣው ዘመን ለራሳቸው ያከማቻሉ:: በምድር ላይ እውነተኛውን ህይወት የሚኖረው ማን ነው? ተስፋቸው እግዚአብሔር የሆነላቸው ባላቸው ሀብት ንብረት የማይመኩ መልካም ሥራ በመስራት ሀብታሞች የሆኑ ከዚህ ዓለም ይልቅ የሚመጣውን ዓለም ተስፋ የሚያደርጉ እነዚህ እውነተኛውን ህይወት ይኖራሉ::

ጌታ ስለ ሀብታሙ ሰው የተናገረው ምሳሌ ያለኝ ጐተራዬ አነሰኝ ሌላ ትልቅ ጐተራ እሰራለሁ ለነፍሱ ነፍሴ ብዙ ሀብት ተከማችቶልሻል ብዬ ጠጭ ተዝናኝ አለ ባለፋት አመታት የሀብታሙ ሰው ምሳሌ ለማያምኑ ሰዎች ለመመስከር እንጠቀምበት ነበር:: አሁን ግን በቤቱ ላለነው የማስጠንቀቂያ መልእክት ነው:: በዚህ ዘመን የምንሰማው ድምፅ ያለኝ ጐተራ አንሶኛል ሌላ ትልቅ ጐተራ እሰራለሁ የሚል ነው:: ወንጌል ሰባኪነትን ሥራህ አድርግ የሚለው ተረስቶ የአብዛኛው ሰው ልብና ዓይን በዙሪያው ባለው ቁሳቁስ ተተክሏል::

እግዚአብሔር ግን አንተ ሞኝ ዛሬ በዚህች ሌሊት ነፍስህን ከአንተ ትወሰዳለች፣ ታዲያ ይህ ያከማቸኸው ሀብት ሁሉ ለማን ይሆናል ለራሱ በምድር ላይ ሀብትን የሚያከማች በእግዚአብሔር ፊት ግን ድኻ የሆነ ሰው እንዲሁ ይሆናል::

በእርግጥ ያለኝ ይበቃኛል የሚል ሰው ፍፁም መንፈሣዊነትን ስለሚያተርፍበት ሃይማኖት የሀብት ምንጭ ነው:: ምክንያቱም ወደዚህ ዓለም ምንም ይዘን አልመጣንም::ከዚህ ዓለም ይዘነው የምንሄደው ምንም ነገር የለም የምንበላውና የምንለብሰው ካገኘን ይበቃናል:: ሀብታሞች ለመሆን የሚፈልጉ ግን በፈተና ይወድቃሉ

ሰዎችን በሚያበላሽና በሚያጠፉ ከንቱና አደገኛ በሆነ በብዙ ወጥመድ ይያዛሉ::ምክንያቱም የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ምንጭ ነው:: አንዳንድ ሰዎች ገንዘብን ለማግኘት በመመኘት ከእምነት ርቀዋል:: ልባቸውም በሐዘን ጦር ወግተዋል:: 1ጢሞ. 6፥6-10

እናንተ አነስተኛ መንጋ የሆናችሁ ወገኖቼ አትፍሩ ምክንያቱም የሰማይ አባታችሁ መንግሥትን ሊሰጣችሁ ፈቅዷል ሉቃ. 12፥32

ጳውሎስ አንድ ጊዜ ወንጌልን ለሰዎች ለመስበክ በውስጡ ይቀጣጠል ነበር:: ተልእኮውን
እንዳያከናውን ፍርሀት ከለከለው:: መፍትሄውን መንፈስ ቅዱስ አመለከተው የፀሎት ርእስ ለወገኖቹ አቀረበ "የወንጌልን ምስጢር ያለ ፍርሀት እንዲገልጥ በሚናገርበት ጊዜ አስፈላጊውን ቃል እንዲሰጠኝ ለእኔ ፀልዩልኝ" ፍርሀት በፀሎት ይርቃል" ::ኤፌ. 6፥19

ከሁሉም በፊት መርሳት የሌለብን ለወንጌል አገልግሎት ከመውጣታችን በፊት በቃሉና በፀሎት መዘጋጀት፣ የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት፣ የምንሄድበትን አቅጣጫ እንዲያሳየን መጠየቅና መዘጋጀት ይኖርብናል:: የእግዚአብሔርን ሥራ ለመስራት ወስኖ የተነሣው ነህምያ ስራውን ከመጀመሩ በፊት ዝግጅት አድርጎአል::

ነህምያ በጊዜው የንጉሥ አርጤክስስ የወይን ጠጅ አሳላፊ ሆኖ ይሰራ ነበር:: መጽሐፈ አስቴር 1፥1-2 መኖሪያው የፋርስ መናገሻ ከተማ በሆነው በሱሳ ያደረገው ንጉሥ አርጤክስስ ከህንድ እስከ ኢትዮጵያ አንድ መቶ ሃያ ሰባት አገሮች ይገዛ ነበር:: የቤተመንግሥቱ ሀብት ስድስት ወር በሙሉ እንዲታይ ያደረገ ባለፀጋ ንጉሥ ነው:: በዚህ ንጉሥ ፊት ለመታየት የሰው ሁሉ ምኞት የነበረበት ዘመን ነው:: እንኳን የመቶ ሃያ አገሮች የሚገዛ ንጉሥ ቀርቶ አንዲት ሀገር የመሩ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አጼ ኀይለ

ሥላሴ ፊት የመቅረብ እድል ያገኙ ከእጃቸው ስጦታ የተቀበሉ በዘመናቸው ሁሉ ይዘክሩታል::

ነህምያ በዚህ ታላቅ ንጉሥ ፊት ሁልጊዜ ይቀርብ ነበር:: በንጉሡና በንግሥቲቱ ዘንድ የሚወደድ ሰው ነበር:: እርሱ ግን የተሻለውን እና መንግሥቱ የማያልፈው እግዚአብሔር ፊት ማየት የለመደ እና የሰለጠነ ስለነበር ምንም አይመስለውም:: ጥሩ ስራ ከተሻለ ደሞዝ ጋር ስላለኝ ይህ መልካም እድል ከእጄ እንዳይወጣ ፀልዩልኝ ብሎ አያውቅም:: የበለጠው በእግዚአብሔር ሥራ አይቶአልና ቅጥሩ የፈረሰ ቢሆንም የእግዚአብሔር ሥራ ቸልተኝነትን ከቶ አላሳየም ነበር::

ከወንድሞቼ ጋር አንዱ ሐናኒ ተብሎ የሚጠራው ሌሎች ሰዎችን አስከትሎ ከይሁዳ ወደ እኔ መጣ:: እኔም ስለ ኢየሩሳሌምና በባቢሎን ምድር ስደት ቆይተው ስለተመለሱት አይሁዳውያን ሁኔታ ጠየቅኋቸው:: እነርሱም ከስደት ተርፈው ወደ ሀገራቸው የተመለሱት አይሁዳውያን በታላቅ ችግርና ሐፍረት ላይ ወድቀው ይገኛሉ የኢየሩሳሌም ቅጥሮችም ፈራርሰው ወድቀዋል የቅጥር በሮቹም በእሳት ጋይተዋል ሲሉ መለሱልኝ:: እኔም ይህን ሁሉ በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስኩ::" ሰዎች በታላቅ ሀዘን ውስጣቸው ሲመታ የሚወስዱት እርምጃ አንድ ብቻ ነው::እርሱም ተዝለፍልፈው መውደቅና መቀመጥ ነው:: የሚቀመጡበት ምክንያት ከሚሰሙት ነገር የተነሣ ሃይል ስለሚያጡ ነው:: የነህምያ ሸክም ከዚህ ነው የጀመረው::

ሥራውን ከመተግበሩ በፊት የዝግጅት ጊዜ ወስዷል በፆምና በፀሎት በንስሃ ስለ ራሱና ስለ ሕዝቡ በእግዚአብሔር ፊት ወድቋል:: ምዕ. 1፥5-7 የሰማይ አምላክ ሆይ አንተ ታላቅ ነህ እኛም በፍርሀት እናከብርሀለን አንተ ከሚወዱህና ትዕዛዝህን ከሚጠብቁ ሁሉ ጋር ቃል ኪዳንህን አፅንተህ ትኖራለህ እግዚአብሔር ሆይ! አገልጋዮችህ

ስለሆኑት የእስራኤል ሕዝብ ደህንነት ቀንና ሌሊት የማቀርበውን ጸሎቴን ስማ:: እኔንም አስበኝ እኛ በእርግጥም እኔና የቀድሞ አባቶቼ በደል ሰርተናል:: በፀሎቱ ከእርሱ በፊት የነበሩት አባቶቹን እያወገዘ አልፀለየም:: ከእነርሱ ጋር እኔም ኀጢአተኛ ነኝ በማለት ራሱንም ጨምሮ ንስሃ ገብቶአል::

በምዕራፍ አንድ የፀለየው ፀሎት በምዕራፍ ሁለት ተመልሶለታል ነህ. 2፥2-5 አንዳች ችግር ቢደርስብህ ነው እንጂ ሳትታመም እንዴት ይህን ያህል ፊትህ ይጠቁራል ሲል ጠየቀኝ እኔም እጅግ በመፍራት ንጉሠ ነገሥቱን ለዘላለም ይኑር የቀድሞ አባቶቼ የተቀበሩባት ከተማ ፍርስራሽ ሆና ስትቀርና የቅጥሮቿም በሮች በእሳት ሲወድሙ እንዴት አላዝንም ስል መለስሁለት ንጉሡም ታዲያ አሁን የምትፈልገው ምንድን ነው? ለጥያቄው ትክክለኛው መልስ ለማግኘት በፀሎት ከአምላኩ ጋር ተነጋግሮ ንጉሠ ነገሥቱን ንጉሥ ሆይ አንተን ደስ የሚያሰኝህ ከሆነና ጥያቄዬን ከተቀበልከው የቀድሞ አባቶቼ ወደ ተቀበሩባት በይሁዳ ወደምትገኘው ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ እንድሄድና ከተማይቱን እንደገና መስራት እንድችል ፍቀድልኝ ብዬ ለመንሁት ንጉሡም ፈቀደለት ወደ ይሁዳ ማለፍ የሚያስችል ደብዳቤ እና ለቤተመቅደስ ቅጥር ለከተማይቱ በር የሚሆን የጥድ ዛፍ ለመቁረጥ ለደን ጠባቂዎች የፈቃድ ደብዳቤ ተሰጠው የጦር መኰንኖች ፈረሰኞች ከእርሱ ጋር እንድሄዱ አደረገ::

ነህምያ ኢየሩሳሌም እንደ ደረሰ ለሦስት ቀን በውስጡ ያለው ራዕይ ለማንም አልተናገረም በሌሊት በአህያው ተቀምጦ የፈረሰውን ተመለከተ ሁሉንም ካየ በኋላ በውስጡ ያለውን ራዕይ ለወገኖቹ ገለጠላቸው እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነው የፈረሰውን የኢየሩሳሌም ቅጥር እንሥራ አላቸው ከመካከላቸው አንድም ሰው እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነው ያለ አልነበረም በዘመናቸው ለምተውት የማያውቁት ድምፅ አሰማቸው::ያ ትውልድ እግዚአብሔርን በታሪክ ነው

የሚያውቁት። እግዚአብሔር ከአብርሃም፣ከሙሴ፣ከኢያሱ፣ከዳዊት ጋር ነበረ የሚል እውቀት ነው የነበራቸው። እግዚአብሔር ከእኔ ጋራ ነው በማለቱ ብቻ ድካም በብርታት ሽንፈት በድል ተተካ በአንድ ልብ እንደገና ስራውን እንጀምር አሉ። እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር መሆኑ በማወቃቸው ብቻ ያለፈውን ጠባሳ ረስተው ሥራውን ለመስራት ተነሱ።

እግዚአብሔር ሆይ ብርሃንህን ትሰጠኛለህ በእኔም ያለውን ጨለማ ታስወግድልኛለህ ጠላቶቼን የምቋቋምበትን ብርታት ትሰጠኛ ለህ። ወደ ምሽጋቸው ዘልዬ እንድገባ ሀይልን ትሰጠኛለህ መዝ. 18፥29-30 ብርታት የሚሰጠኝ መንገዴን የሚያቃናልኝ እግዚአብሔር ነው እርሱ እግሮቼን እንደ ብሖር እግሮች ያጠነክራል። በከፍታ በታዎችም ላይ በሰላም ያኖረኛል። እጆቼን ለጦርነት ያሰለጥናል የነሐስን ቀስት መሳብ እንድችል ክንዶቼን ያበረታል።

## የነህምያ ጽናት ምሥጢር፡-

እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነው ንጉሱም መልካም ነገር ነግሮኛ ል ያለው ነህምያ ሥራውን ለመጀመር በተነሳ ጊዜ እንግዳ ነገር ገጥሞታል። ልብን የሚያዝል እርምጃ የሚገታ የፈጠጠ ችግር አጋጠመው በዚህ ጊዜ እቃውን ጠቅልሎ ትቶአቸው ወደ ቀድሞ ሥራው አልተመለሰም። ወደኋላ ከመመለስ ይልቅ

ሀ. <u>በእግዚአብሔር መታመኑ</u>

ነገር ግን ሰንበላጥና ጦቢያ እንዲሁም ጌሼም ተብሎ የሚጠራው አንድ የዐረብ ተወላጅ እኛ ያወጣነውን የሥራ እቅድ በሰሙ ጊዜ በእኛ ላይ እየዘበቱ በመሳቅ ስለ ምትሰሩት ነገር ምን ታስባላችሁ? ወይስ በንጉሥ ነገሥቱ ላይ ማመፅ ትፈልጋላችሁ? ሲሉ ጠየቁን እኔም የሰማይ አምላክ ሥራችንን ለማከናወን ይረዳናል። እናንተ ግን

በኢየሩሳሌም ምንም አይነት ንብረት የማግኘት መብት ሆነ የታሪክ መታሰቢያነት አይኖራችሁም ብዬ መለስኩላቸው::

እነዚህ ሰዎች ባለ ስልጣናት ናቸው በስልጣናቸው ተጠቅመው ሊገድሉኝ ይችላሉ የሚል ፍርሀት ሳይሰማው መልስ ሰጣቸው:: እኔም መልሼ ብሎ ይጀምራል:: አገልጋይ በሕይወቱ ለሚሰማው ዛቻ መልስ የማይሰጥ ከሆነ በሚሳኤል ተመቶ እንደ ተከሰከሰ ጀት ይቆጠራል:: ሰይጣን መንፈሳዊ አካልን የሚያፈርስ ፍላፃ ይልካል እንደ ነህምያ መልስ መስጠት አለብን :: መጽሐፍ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙት ከእናንተም ይሸሻል ያዕቆብ 4፥7 ሰይጣንን የምንቃወምበት የመጀሪያው መሣሪያ ለእግዚአብሔር መገዛት ነው::

በእርሱ ግዛት ውስጥ መመላለስ ከጨለማው ዓለም ጋር አለመተባበር ብርሀን የሆነውን ክርስቶስን መልበስ:: በሰይጣን ግዛት ውስጥ ገብቶ ሰይጣንን መቃወም አይቻልም በጨለማ ውስጥ ያለ ጨለማን መቃወም አይችልም በብርሀን ያለ ሰው ጨለማን መቃወም ይችላል::

በኑሮአችን ዲያብሎስን ሳንቃወም በአንደበት እንቃወማለን ብንል አይሆንም በኑሮአችን ሰይጣንን እየተቃወምን በአንደበት አለመቃወም ትክክል አይደለም ሁለቱንም መጠቀም አለብን::

ነህምያ ለወገኖቹ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነው ብሎ አውጆ ነበር:: ይህን ቃል ለጠላቶቹም ሲያውጅ ነው የምናየው:: የጠላቶቹን ቃል እያሰላሰለ አልሄደም የሚያሰላስሉት ቃል ሰጣቸው እንጂ እናንተ ግን በኢየሩሳሌም እድል ፈንታ መብት የላችሁም አላቸው::

የእኛ ግን ከዚህ የተለየ ነው፤ ለወንድሞችና ለእህቶች እግዚአብሔር ከኛ ጋር መሆኑን አስረግጠን እናውጃለን ከጠላት ጋር በጦር ሜዳ ስንገናኝ የእርሱ አዋጅ ብቻ ነው ተግባራዊ የሚሆነው እግዚአብሔር ከአንተ ጋር አይደለም:: ከአንተ ጋር ቢሆን እነዚህ ሁሉ

ነገሮች በሕይወትህ አይከሰቱም ነበር። እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር የሆኑት አትመለከትም እንዴት እንደ ተሳካላቸው ሲለው እንደ ነህምያ እኔም መልሼ አይልም ራሱን እየነቀነቀ አምን ትክክል ነው ይላል።

ጌታ እንዲህ ብሎናል "እንግዲህ ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው የእኔ ደቀመዝሙር አድርጓቸው። ያዘዝኋቸውንም ሁሉ እንዲፈፅሙ አስተምሩአቸው እነሆ እኔ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ ማቴ. 28፥19-20 ምናልባት እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ የሚለው ይገልፀው እንደሆነ ልመስክርላችሁ በልጅነቴ በሜዳ ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል ካለፈብኝ በአጠገቤ የወደቀ ግንድ ወይም ቁጥቋጦ ስመለከት አስፈሪ አውሬ መስሎ ነው የሚታየኝ ዘሎ አንዳች ነገር ያደርገኛል ብዬ እፈራ ነበር ጨለማ የራሱ የሆነ መልእክት አለው። አባቴ ከእኔ ጋር በሚሆንበት ጊዜ ቁጥቋጦ የፈለገውን ያህል መልኩን ቢለውጥ ሌላው ቀርቶ ጅብ እንኳ ከሙኸ አልፈራም በአባቴ ትከሻ ሆኜ እንዲያሳየኝ እጠይቀዋለሁ እንጂ።

ብዙዎቻችን በፊታችን የወደቀ ግንድ አይተን ተደናግጠናል። ፀሎትና ቃሉን አቁመናል አገልግሎት ትተናል። ነህምያ በጠላቶቹ ፊት የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል ያለው መከናወን የሚሰጥ ከታች ሳይሆን ከላይ መሆኑን ስለተረዳ ነው ።

ለ. <u>የነህምያ ፀሎት</u>

የቅጥሩን ግንብ ሥራ መጀመራችንን ሰንበላጥ በሰማ ጊዜ በጣም ተቆጣ ተበሳጭቶም ሊዘባበትብን ተነሣ ነህ.4፥1 የጠላትን ቁጣ የምናከሽፍበት መሣሪያ ፀሎት ነው።

ባህርን በኀይልህ የከፈልህ አንተ ነህ የባህሩንም አውሬ ራሶችን በውሀ ውስጥ ቀጠቀጥህ የሌዋታንን ራሶችን አደቀቅህ ለምድረ በዳ

ፍጥረታትም ምግብ አድርገህ የሰጠሃቸው ምንጮችንና ፈሳሾችን ያፈለቅህ አንተ ነህ መዝ. 74፥13-14

ፀሎት ማለት የአውሬውን ራሶች ማፍረስ ማለት ነው። ራስ አስተሳሰብን የሚወክል ነው። በፀሎታችን ጊዜ የሰይጣንን ሀሳብ ነው የምናፈርሰው።እርሱ የገዦች መንፈስ ይሰብራል። መዝ 76፥12 ፀሎት የዚህ አለም ገዥ መንፈስ መስበር ነው።

- ***ፀሎታችን ሦስት ነገርን ያከናውናል።***

1. የሌዎታንን ራስ ያደቅቃል መንፈሱን ይሰብራል
2. ምንጮችን ያፈልቃል
3. ምድረ በዳውን ያለመልማል

"የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ ተነስ ሀይልን ልበስ እንዳለፋት ዘመናት በጥንት ትውልዶችም እንደሆነ ነው ሁሉ ተነሥ ረዓብን የቆራረጥክ ታላቁን ዘንዶ የወጋህ አንተ አይደለህምን? የዳኑት እንዲሻገሩት ባህሩን የታላቁንም ጥልቅ ውሆች ያደረቅህ በጥልቁ ውስጥ መንገድ ያበጀህ አንተ አይደለህምን?" ኢሳ. 51፥19-10

አባቴ ሁለት ሚስቶች ነበሩት ሁለቱም የራሳቸው ቤት ነበራቸው በተጨማሪም በግቢያችን ሌሎች ዘመዶቻችን ቤት ሰርተው ይኖሩ ነበር። በሰፊው ግቢ በዛ ያሉ ቤቶች ነበሩ ከቤታችን በስተኋላ ሰፊ የአትክልት ቦታ ነበር። አባቴ ጫት እየኮተኮተ ሳለ በጣም ትልቅ እባብ በአጠገቡ ያልፋል ጠብቆ አንዴ መታው በኀይል ተቆጥቶ እያፏጨ ከአንዱ ቤት ሌላው ቤት እየተወረወረ ግቢውን አወከው በሌላ መንደር ይኖር የነበረው የእንጀራ እናቴ የቅርብ ዘመድ በሀይል ስላመመው በተዘጋጀለት ማረፊያ ተኝቶአል የቁርዓን አስተማሪያችን ነበር አባቴ እባቡን ለመምታት ቀረበ እባቡም ከበፊቱ የበለጠ ተወርውሮ ለመንደፍ ተዘጋጅቶአል። የቁርዓን አስተማሪያችን ሰምቶ

ከተኛበት ተነስቶ መጣ በሀይል ቃል ተው አትንካው አንተን ፈልጐ አልመጣም እኔን ነው እንጂ አለ፡፡

ወዲያው በትልቅ ገል እጣን አጨሰለት ወደ እርሱ ቤት ቀጥታ ሄደ ወደዚያና ወደዚህ ውር ውር አትበሉ የሚል ትዕዛዝ ስለ ተሰጠን ግቢውን ትተን ወጣን ከዚያ በኋላ ሰውየው ብዙም አልቆየም ወዲያው ነው የሞተው ያ እባብ በሌላ ጊዜ ከእኛ አጥር ዝቅ ብሎ ባለው ጫካ እየተሳበ ይሄድ ነበር ፡፡ ወፎችም እርሱን እየተከታተሉ ይንጫጩ ነበር፡፡ እባቡም ምፎቹን ለመያዝ ይሞክር ነበር፡፡ እንዳለፈው ግርግር ሳይፈጥር አድፍጦ ጠበቀው እሾህ የሚሽከምበት ባላ በእጁ ይዞአል፡፡ እባቡ ሳያየው ጭንቅላቱን ወግቶ ከመሬት ጋር አጣበቀው ጭንቅላቱ ተወግቶ ፈራርሶ ሞተ፡፡

ከዚህ በኋላ ጌታ ሌሎች ሰባ ሁለት ሰዎችን መርጦ ሾመ ወደ ሚሄድበትም ከተማና ቦታ ሁሉ እንዲቀድሙት ሁለት ሁለት አድርጐ ላካቸው እንዲህም አላቸው መከሩስ ብዙ ነው ሠራተኞቹ ግን ጥቂት ናቸው፡፡ ስለዚህ የመከሩ ጌታ ሠራተኞችን ወደ መከሩ ቦታ እንዲልክ ለምኑት እንግዲህ ሂዱ እንደ በጐች በተኩላዎች መካከል እልካችለሁ፡፡ ሰባ ሁለቱም ደስ እያላቸው ተመልሰው ጌታ ሆይ አጋንንት እንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት፡፡ እርሱም እንዲህ አላቸው ሰይጣን እንደመብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ፡፡ እንግዲህ እባቡንና ጊንጡን እንድትረግጡ በጠላትም ሀይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ የሚጐዳችሁም አንዳች ነገር አይኖርም፡፡ ይሁን እንጂ መናፍስት ስለተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ ስማችሁ ግን በሰማይ ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ፡፡ ሉቃ. 10፣1-3፣17-20

እኛ ወንጌልን ለመስበክ ስንወጣ ጌታም አብሮን ይወጣል ወደ ምንወጣበት አቅጣጫ ጌታ አንድ ነገር ይመለከታል፡፡ ይኸውም የአካባቢው የአየር ላይ ገዥ መንፈስ ከሰማይ እንደ መብረቅ ስወድቅ ያያል፡፡

ሰንበላጥ የተበሳጨው የቅጥሩን ሥራ መጀመር ሰምቶ ነው:: ሰይጣን አንድ ሰው ሲጠጣ ሲያጨስ ዝሙት ሲሰራ የሰው ህይወት ሲያጠፋ ቢያየው ደስታው ነው:: ነገር ግን በንስሃ በጌታ ኢየሱስ አምኖ ህይወቱ መስተካከል ሲጀምር በቃሉ በፀሎትና በወንድሞች ህብረት ህይወቱ መገንባቱን ሲያይ በዚህ ጊዜ መወራጨት ይጀምራል::ሰንበላጥ በብዙ አቅጣጫ የነህምያ አገልግሎት ለማሰናከል ሞክሮአል:: መስዋዕት በማቅረብ ሥራውን በአንድ ቀን ለመፈፀም የምትችሉ ይመስላችኋልን? አይሁዳውያን ለእግዚአብሔር መስዋዕት በማቅረብ የጀመሩት ሥራ እንደ ማይሳካላቸው እርግጠኛ ሆኖ ተናገረ:: መሰውያው ከህይወታቸው ጋር የተቆራኘ ነው:: በአጠገቡ ቆሞ የነበረው ጦቢያም በበኩሉ እነርሱ ምን ዓይነት ቅጥር መሥራት ይችላሉ? የእነርሱ ግንብ ቀበሮ እንኳ ብትወጣበት ይፈርሳል::

ፀሎት እንዲህ ዓይነት ተግዳሮት ድል የምናደርግበት መሳሪያ ነው:: እኔም እንዲህ ስል ፀለይሁ አምላክ ሆይ እንዴት እንደሚሳለቁብን ተመልከት ይህም ስድባቸውን በራሳቸው ላይ ይምጣባቸው ያላቸው ሀብትና መብት ሁሉ ተገፈው በባዕድ አገር ስደተኞች ይሆኑ ስለሚያደርጉት ክፋት ምህረት አታድርግላቸውም:: የፈረሰውን በመስራታችን በስድብ አዋርደውናልና በደላቸውን አትርሳ:: የነህምያ ፀሎት የተጀመረው ቅጥር እንድቀጥል አድርጓል የእኛም ጅማሬ ዳር እንዲደርስ ቅጥሩን እየሰራን መፀለይን መርሳት የለብንም::

ስለዚህ በአንድነት ተባብረው ወደ ኢየሩሳሌም ለመምጣትና አደጋ ጥላው ሽብር ለመፍጠር በእኛ ላይ አድማ አደረጉ እኛ ግን ወደ አምላካችን ፀለይን እነርሱም ለመቋቋም ሌሊትና ቀን ቆመው የሚጠብቁ ዘበኞችንም መደብን:: በእኛም አገልግሎት የሰይጣንን ክፉ ሀሳብ የሚያፈርሱ ቀንና ሌሊት የሚማልዱ ሰዎች አብረውን በሥራው መሰለፍ አለባቸው:: ዛቻ በታን ያስለቅቃል ኤልያስ

ብቻውን ባይሆን ኖሮ አገልግሎቱን ጥሎ ርቆ ባልሄደ ነበር። ነህምያ 4፥8-9

በየቤተሰባቸው በመመደብ ቦታቸው እንዲይዙ አረግሁ ይላል መንፈሳዊ አገልግሎት ከቤት ይጀምራል። ቤተሰቡ የፈረሰበት አገልጋይ ውጤታማ አገልግሎት መስጠት አይችልም ራስንና ቤተሰብን በፀሎት መቅጠር በደሙ መሸፈን የጠላትን ቀስት አቅጣጫውን ስቶ እንድሄድ ያደርጋል።በህዝ. 40፥5 ቤተመቅደሱን ዙሪያ ሙሉ በሙሉ የከበበ ቅጥር አየሁ።

ስለታም ሰይፍ በእጃቸው ይዘው፤ እልል እያሉ እግዚአብሔርን በከፍተኛ ድምፅ ያመሰግኑ መዝ. 149፥6

እኔ ራሴ በዙሪያዋ የእሳት ቅጥር እሆንላታለሁ ይላል እግዚአብሔር በውስጧም ክብሯ እሆናለሁ ዘካ.2፥5

ሐ. <u>*እግዚአብሔርን ማሰቡ*</u>

ነገሩን በጥሞና ከተመለከትሁ በኋላ መኳንንቱን ሹማምንቱና የቀረውን ሕዝብ አትፍሯቸው ታላቁንና የተፈራውን እግዚአብሔር አስቡ። ነህምያ 4፥14 አባትና ልጅ ከእርሻ ወደ ቤት ሲመለሱ ዝናብ ዘንቦ ኑሮ የሞላ ወንዝ ገጠማቸው ይቀንሳል ብለው ብዙ ጠበቁ አልቀነሰም ሳይጨልም መሻገር ስለነበረባቸው አባትየው ልጁን በትከሻው ተሸክሞት ወደ ወንዝ ገቡ በቀስታ እየተራመደ ሳለ በሀይል የሚወናጨፈውን ጉርፍ ተመልክቶ ልጅየው ሊወስደን ነው ወደ ኋላ እንመለስ አለ አባትየው ወደ ውሃው አትመልከት ወደ ሰማይ ተመልከት አለው።

ነህምያ በሕይወቱ የተለማመደው ነገር ቢኖር በዙሪያው ካለው ችግር ባሻገር ታላቁ እግዚአብሔርን ማሰብ ነው ሕዝቡ በየዕለቱ ከሚሰማው ወሬ የተነሣ የፈራረሰውን ለማንሳትና ለመገንባት ሀይል አጡ። ከፍርሀት የተነሣ ወገቡን የሚይዘው ሰው በዛ ሁሉም

ጠላቶቻቸው ያሰሙአቸው ዛቻ እያሰቡ ተክዘዋል:: ይህን የተመለከተው ነህምያ እንዲህ አለ ሕዝቡንም ባለሥልጣኖች ሁሉ ከጠላቶቻችን የተነሣ አትፍሩ ምን ያህል ታላቅና ግርማው የሚያስፈራ አምላክ እንዳለን አስቡ እርሱ ስለወገኖቻችሁ ስለ ልጆቻችሁና ሚስቶቻችሁ ስለ ቤት ንብረታችሁም እንደ ሚዋጋላችሁ አስታውሱ አልኋቸው አዘውትሮ ስለ ሰይጣን ታላቅነትና ሀያልነት የሚሰማ ጉባኤ ስለ ሰይጣን ክፉ ስራ እያሰላሰሉ ይወጣሉ ያ ጉባኤ ፍርሀት በውስጡ ስላለ ወንጌል ለሌላው ማድረስ ቀርቶ ለራሱ መንገድ ጠፍቶበታል:: ሥራው እንዲቀጥል ያደረገው ሕዝቡ የአስተሳሰብ ለውጥ ስለአደረገ ነው :: ነህምያ ከማሳሰቡ በፊት እስራኤል ሁሉ የሚያስበው ሚስቶቻቸው ጭካኔ በተሞሉ ወታደሮች ሲደፈሩ ሲደበደቡ ልጆቻቸው ከቤተሰብ ተነጥለው ወደ ባእድ ሀገር በምርኮ ሲወሰዱ ንብረታቸው ሲዘረፍ ከብቶችና በጉቻቸው በጠላቶች ተነድተው ሲወሰዱ ያሳለፉት የሥቃይ ኑሮ ተመልሶ እንደ መጣባቸው በእነርሱ አስተሳሰብ አረጋግጠው ጨርሰዋል:: በውስጣቸው የተቀመጠው የሽንፈት አስተሳሰብ መለወጥ ነበረበት:: ታላቅ ግርማው የሚያስፈራ አምላካችሁ እግዚአብሔር ስለ ወገኖቻችሁ፣ ስለሚስቶቻችሁ ስለ ቤት ንብረታችሁም እንደ ሚዋጋላችሁ አስታውሱ አላቸው:: ይህ ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ከሽንፈት አውጥቶአል:: ለአንድ አላማ መሳካት ወይም አለመሳካት መሪ ወሳኝ ነው የሚባለው ለዚህ ነው:: ይህ ቆራጥና በእግዚአብሔር የሚታመን በወገኖቹ የነበረውን ፍርሀት መንግሎ አወጥቶ ስለ እነርሱ የሚዋጋው የእግዚአብሔርን እንዲያስቡ አድርጎአል::

ጠላቶችንም የተማማሉበትን አድማ የደረስንበትን መሆኑ ሰሙ እግዚአብሔርም እቅዳቸውን እንዳከሸፈባቸው ተገነዘቡ ከዚያ በኋላ ሁላችንም የቅፅሩን ግንብ መሥራታችንን ቀጠልን::

የአዲስ ኪዳን መመሪያ ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን የሚያምን ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነው:: "አባቱንም የሚወድድ ሁሉ ልጁንም ይወዳል:: እግዚአብሔርን የምንወድድ መሆናችንን የምናውቀው እግዚአብሔርን ስንወድድ ትዕዛዞችን ስንፈፅም ነው :: እግዚአብሔርን መውደድ ማለት ትዕዛዞችንም መፈፀም ነው ትዕዛዞቹም አስቸጋሪዎች አይደሉም:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ሁሉ ዓለምን ያሸንፋል ዓለምን የምናሸንፈው በእምነታችን ነው::
ዓለምን የሚያሸንፈው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚያምን ብቻ ነው"::1ዮሐ. 5፥1-5

የእግዚአብሔር መሆናችን ብቻ አሸናፊ እንደሚያደርገን ታውቃላችሁ ይህን ሀሳብ ከመግለፄ በፊት አንዳንድ ጥያቄዎች ላንሣ

- በዓለም ላይ ምን ያህል ነቢያቶች ተነስተዋል?
- ከእግዚአብሔር መሆናቸውና አለመሆናቸውን እንዴት እናውቃለን?
- ሐሰተኛ ነቢያት የምናሸንፈው እንዴት ነው ?
- ወንጌልን ለሌሎች ለመመስከር ወጥተህ ከተነሳብህ ጥያቄ የተነሳ እምነትህን ተጠራጥረህ ታውቃለህ ?

ከላይ ለተነሱት ጥያቄዎች መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ መልስ አለው:: 1ዮሐ. 4፥1-6 ወዳጆች ሆይ በዓለም ላይ ብዙ ሀሰተኞች ነቢያት ስለተነሱ መንፈስን ሁሉ አትመኑ ይልቅስ ሌሎች መናፍስትንና የእግዚአብሔር መንፈስ ለይታችሁ የምታውቁት እነሆ በዚህ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በሥጋ መገለጡን የሚመሰክር መንፈስ ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በሥጋ መገለጡ የማይመሰክር መንፈስ ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ አይደለም :: ይህ መንፈስ ይመጣል ሲባል የሰማችሁት የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ነው እርሱ አሁን እንኳ በዓለም ላይ አለ::"

ወዳጆች ሆይ እናንተ የእግዚአብሔር ናችሁ። በእናንተ ያለው መንፈስ በዓለም ካለው መንፈስ ይበልጣል። ስለዚህ ሐሰተኞች ነቢያት አሸንፋችኋል። እነርሱ የዓለም ናቸው የሚናገሩትም የዓለም ነገር ነው። ዓለም እነርሱን ይሰማቸዋል። እኛ የእግዚአብሔር ነን እግዚአብሔርን የሚያውቅ ሁሉ ይሰማናል። የእግዚአብሔር ያልሆነ ግን አይሰማንም፤ እውነተኛ መንፈስና ሐሰተኛ መንፈስ ለይተን የምናውቀው በዚህ ነው።

ከጥንት ጀምሮ በሐዋርያት ዘመን በተለይም ከሐዋርያቶች በኋላ ብዙ ፅድቅ ፈላጊዎች በሐሰተኞች ነቢያት ተታለዋል። አሁንም እየሳቱ ነው ዩሐንስ የሰጠው ማስጠንቀቂያ መልእክት ቢሰሙ ኖሮ ብዙዎች ከሞት ወጥመድ ባመለጡ ነበር።

የሐሰት ትምህርት አነሳስ የክርስቶስን በሥጋ መወለድ በመካድ ወይም መለኮትነቱን ባለመቀበል ነው።

ጌታ ለእኛ ብሎ ሁሉን ተወ፤ ከአብ ጋር እኩል የሚያደርገው የመለኮት ባህርይ እንደያዘ መቅረት አልፈለገም በመስቀል ተሰቅሎ እስከ መሞት ታዛዥ ሆነ ወልድ የሰው ልጅ ስለሆነም እንዲፈርድ ሥልጣን ሰጥቶታል። ዮሐ. 5፣27 ራሳቸውን የጆሆቫ ምስክር ብለው የሚጠሩ በመጀመሪያ ኢየሱስ አምላክ አይደለም አሉን። አምላክ መሆኑን የሚናገረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስናሳያቸው ኀያል አምላክ ነው እንጂ ሁሉን ቻይ አምላክ አይደለም አሉ። ይህን አባባላቸውን የሚያፈርስ ሁሉን ቻይ አምላክ መሆኑን ሲያገኙ የዘላለም አምላክ አይደለም እያሉ ነው። ዘላለማዊ አምላክ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልፅ ይናገራል።

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ሰውን በመልካችንና በአምሳያችን እንፍጠር፤ ሰዎችም በባህር ውስጥ በሚኖሩ ዓሣዎች፣ በሰማይ በሚበሩ ወፎች፣ እንስሳትና በምድር ላይ በደረታቸው እየተሣቡ

በሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶች እንዲሁም በምድር ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራቸው አለ። እግዚአብሔርም ብዙ ተባዙ ዘራችሁም ምድርን ይሙላ ምድርም በቁጥጥራችሁ ስር ትሁን በባህር ውስጥ ዓሣዎች የሰማይ ወፎች እንዲሁም በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሕያዋን ፍጡር ሁሉ ግዟቸው ብሎ ባርካቸው። ዘፍ. 1፥26-28

ለሰው ሥልጣን የሰጠው እግዚአብሔር ነው። ወልድ የሰው ልጅ ስለሆነ ከአብ ሥልጣን ተሰጥቶታል። አዳም ሥልጣን ከእግዚአብሔር እንደተቀበለ ሁሉ ወልድም እንዲሁ ተቀብሎአል እንፍጠር በሚለው የምክር ቃል ተካፋይ የነበረ ሰውን የፈጠረ አምላክ ሰው ሆነ እንደ ሰው ሥልጣን ከሌላው አካል መቀበል ነበረበት፣ ልክ እንደ አዳም። ይህን ካለመረዳት ብዙዎች ስለ ክርስቶስ ያላቸው አስተምህሮ ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር የማይስማማ ነው።በጌታ በኢየሱስ አምነው ዳግም የተወለዱ በዓለም ያለውን መፍራትና መጨነቅ የለባቸውም።

ልጆች ሆይ እናንተ የእግዚአብሔር ናችሁ በእናንተ ያለው መንፈስ በዓለም ካለው መንፈስ ይበልጣል ስለዚህ ሐሰተኞች ነቢያትን አሸንፋችኋል።

መ. <u>ዋጋ ለመክፈል የተዘጋጀ ሰው መሆኑ</u>

በዚህ ጊዜ ከቤቱ እንዳይወጣ ተዘግቶበት ወደነበረው የመጣብኤል የልጅ ልጅ ወደ ሆነው ወደ ደለያ ልጅ ሸማዕያ ዘንድ ሄድሁ እርሱም በማናቸውም ሌሊት ሊገድሉህ ስለሚመጡ አንተና እኔ ወደ እግዚአብሔር ቤተመቅደስ ውስጥ ገብተን በሮቹን በመዝጋት እንደበቅ አለኝ። እኔ ግን እንደ እኔ ያለው ሰው ሸሽቶ አይደበቅም በቤተ መቅደስ ውስጥ ተደብቄ ሕይወቴን ለማዳን እንደምፈልግ አድርገህ ታስባለህ? ይህን ከቶ አላደርገውም ስል መለስሁለት። ነህ. 6፥10-11 ሸማያ ካህን ነው፣ የሚኖረውም በቤተ መቅደስ ነው። ነገር

ግን መሰዊያውንና ከመጋረጃው በስተ ውስጥ በኩል ያለውን ቅድስተ ቅዱሳኑን የሚመለከተውን የክህነት ሃላፊነት የምትፈፅሙ አንተ እና ልጆችህ ብቻ ናችሁ፣ የክህንነት አገልግሎት እድል ፈንታ አድርጌ ስለ ሰጠኋችሁ ይህን ሁሉ ሀላፊነት የእናንተ ነው:: ሌዋዊ ያልሆነ ማንኛ ው ሰው ወደ ንዋያተ ቅዱሳት ቢቀርብ ይሞታል:: ዘኁል.18፥7

ሸማያን ጦቢያና ሰንበላጥ በገንዘብ ገዝተውት ነበር "የልባቸውን ምኞት ለመፈፀም ነህምያን በእጃቸው አሳልፎ ለመስጠት የተስማማ ሰው ነው:: ነህምያ ወደዚህ ሰው ለምንድን ነው የሄደው? በዚያን ዘመን ሰዎች ወደ ካህን ለተለያዩ ጉዳዮች ይሄዱ ነበር:: የኀጢአት መሥዋዕት እና የምስጋና መሥዋዕት ለማቅረብ ከእግዚአብሔር ምህረት ለመቀበልና ድምፁን ለመስማት ይሄዳሉ:: ነህምያ ለእግዚአብሔር ራሱን ከለየው ካህን የእግዚአብሔርን ድምፅ ለመስማት ነበር አካሄዱ፣ ካህኑ ሸማያ ግን በገንዘብ ተገዝቶ ነበር::

በአሁኑ ዘመንም ሰዎች የእግዚአብሔርን ድምፅ ለመስማት ወደ ነቢያት ይሄዳሉ:: እንደ ሸማያ ክህነቱን በገንዘብ የለወጠ ነቢይ እግዚአብሔር ያላለውን ብሎአቸው ለመፅናናት ናፍቀው የተገላብጦሽ በሀዘናቸው ላይ ሀዘን ጨምረው ምነው ወደዚያ ሰው ባልሄድሁ ብለው በፀፀት የሚናገሩ ብዙ ናቸው" ያልተሸቃቀጠ ኩልል ያለ የእግዚአብሔር ድምፅ በወንድሞች ህብረት መስማት አልተቻለም:: በጊዜያአዊ ጥቅም ብዙዎች ክህነታቸውን ለውጠውታል ከራሳቸው ምኞት ተነስተው መንፈስ ቅዱስ ሳይናገራቸው እግዚአብሔር እንዲህ ይላል የሚሉ አሉ :: ደግሞ እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ድምፅ የሚያስተላልፉ አሉ:: አላማዬ የዘመናችን የሸማያ መንፈስ አሠራር ለመግለፅ ስላልሆነ በዚሁ ልለፈው ::

ሸማያ እውነተኛውን የእግዚአብሔር ድምፅ መስማት ይችላል:: ካህንነውና ከአሮን ዘሮች የእግዚአብሔር ድምፅ ሩቅ

አይደለም፡፡ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ሕዝብ እንዲህ ይላል ነቢያቱ የሚሉትን አትስሙ እነርሱ በሐሰተኛ ተስፋ ይሞሏቹኋል የሚነግሩአችሁን በአሳባቸው ያለሙትን እንጂ እኔ የምነግራቸውን ቃል አይደለም የእኔን ቃል መስማት የማይፈልጉትን ሕዝቦች አይሏአችሁ ሰላም ይሆንላችኋል ይሉአቸዋል እልኸኛ የሆነውንም ሁሉ አይዞህ ምንም መቅሰፍት አይደርስብህም ይሉታል እኔ እንዲህ አልሁ ከእነዚህ ነቢያት መካከል የእግዚአብሔርን ምስጢራዊ ሀሳብ የሚያውቅ አንድ እንኳ የለም፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ያስተዋለ ወይም ልብ ብሎ ያዳመጠ አንድ ስንኳ የለም፡፡ የእግዚአብሔርን ቁጣ በክፉዎች ራስ ላይ እንደሚተም ማዕበልና እንደ ብርቱ አውሎ ነፋስ ነው ያቀደውንም ሁሉ እስኪፈጽም ድረስ ከቶ አይገታም ወደ ፊት ሕዝቡ ይህን ሁሉ በግልጥ ይረዱታል፡፡ኤር. 23፥16-20

ሽማያ እኔ ከዳንኩኝ ስለሌላው ሰው ምን ቸገረኝ የሚል መንፈስ ነው ያለው፡፡ በማናቸውም ሌሊት ሊገድሉህ ስለሚመጡ አንተና እኔ ወደ እግዚአብሔር ቤተመቅደስ ውስጥ ገብተን በሮቹን በመዝጋት እንደበቅ አለኝ፡፡ የኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ የህዝቡ መከራና ስቃይ ለሽማያ ጉዳዩ አይደለም፡፡ ራሱን ካዳነ የወገኖቹ መከራ አይመለከተውም በቤቱ ያለነው የሽማያ መንፈስ በቁጥጥሩ ስር ያደረገንነው የሚመስለኝ፡፡ ራሱን በቤተ መቅደስ የሚሸሽግ ትውልድ እኔ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኛለሁ ስለ ሚጠፋውና ስለ ሚድነው እኔን አያስጨንቀኝም በማለት ሁሉም የራሱን ምድራዊ ኑሮ እየኖረ ነው፡፡

ሽማያ ነህምያን የሚያሰናክልበት ሙሉ ትጥቅ ነበረው፡፡ ግን አላማው አልመታለትም፡፡ እኔ ግን እንደ እኔ ያለ ሰው ሸሽቶ አይደበቅም በቤተመቅደስ ውስጥ ተደብቄ ሕይወቴን ለማዳን እንደምፈልግ አድርገህ ታስባለህ? ይህን ከቶ አላደርገውም ስል

መለስሁለት:: ከሕይወቱ ይልቅ የሚመራውን ህዝብ የመረጠ አገልጋይ በታላቅ መከራ የነበረውን የእስራኤል ሕዝብ መቼ መሸሸጊያ አገኘ በጨለማ ያለው ሕዝብ መቼ ዳነ ሕዝቤን ከመከራ ለማውጣት ነው ሁሉን ትቼ የመጣሁት አለ::

ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ አደገበት አገር ወደ ናዝሬት ሄደ እንደልማዱም በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ ገባ ሊያነብም ተነሣ የነብዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ ተሰጠው መጽሐፉን በገለጠ ጊዜ እንዲህ ተብሎ የተጻፈበትን ቦታ አገኘ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው መልካም ዜናን ለድኾች እንዳበሥር ሾሞኛል ለታሰሩት መፈታትን ለታወሩት ማየትን እንዳውጅና የተጨነቁትን ነፃ እንዳወጣ ልኮኛል:: እንዲሁም እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያድንበት የፀጋ ዓመት እንዳስታውቅ ልኮኛል:: ሉቃ. 4፥16-19

ነህምያ በሕይወቱ ተወራርዶ የፈረሰውን አድሷል የእስራኤልን ሕዝብ ከነበረበት መከራ ነፃ አውጥቶአል:: የአዲስ ኪዳን አገልጋይ የሆነው ጳውሎስ ስለ ወንጌል እስከ ሞት መዘጋጀቱን ሲገልፅ እንዲህ ብሎአል:: ነገር ግን ለእኔ ረብ የነበረው ሁሉ ስለክርስቶስ እንደ ጉዳት ቆጥሬዋለሁ አዎን በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቆጥራለሁ ስለ እርሱ ሁሉን ተጐዳሁ ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ በክርስቶስ በማመን ያለው ፅድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ እንጂ ከሕግ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደጉድፍ እቆጥራለሁ እርሱንና የትንሳኤውን ኀይል እንዳውቅ በመከራውም እንድካፈል ወደ ሙታን ትንሳኤ ልደርስ ቢሆንልኝ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ ፊሊ.2፥7-11 ሐዋርያቶች ፈሪዎች ነበሩ በዚያች በጌታ የመከራ ሌሊት አንድ ሰውም በአጠገቡ የቆመ አልነበረም ሁሉም ትተውት ሸሹ ድክመታቸውን የሚያውቅ ጌታየተስፋ ቃል ሰጣቸው እነሆ እኔ

የአባቴን የተስፋ ስጦታ እልክላችኋለሁ::እናንተም ኀይል ከላይ እስኪሰጣችሁ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ ሉቃ. 24:49

ሰባኪው በእሁድ አምልኮ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ በሚል ርእስ ሰበከ ሰባኪው በንግግሩ መሀል መንፈስ ቅዱስ ያልተሞላ ወንጌልን መስበክ አይችልም በመንፈስ ቅዱስ ኀይል መሞላት አለባችሁ ብሎ ተናገረ:: ዳንኤል ወደ ጌታ ከመጣ ሁለት ዓመት ሆኖታል የዳንኤል ጓደኛ አቤኔዘር ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ላልዳኑት ሰዎች ወንጌልን ይሰብካል:: ጊዜው ክረምት ነበርና ዳንኤልን ለመጠየቅ ወደ ቤቱ ሄደ አግኝቶ እንደምን አለህ? ሕይወት እንዴት ነው? የፀሎት ጊዜ ከጌታ ጋር አለኝ ቃሉን ሳጠና ውስጤ ይቀጣጠላል እግዚአብሔር ቃሉን እየገለጠልኝ ነው አለው:: ነገ ለምስክርነት አብረን ብንወጣ ምን ይመስልሀል? አለው ያለፈው እሁድ የተሰበክነውን ስብከት አልሰማህም በመንፈስ ቅዱስ ያልተሞላ ሰው ወንጌልን መስበክ አይችልም ተብሎአል:: እኔ እኮ በመንፈስ ቅዱስ አልተሞላሁም ሌሎች በልሳን ሲፀልዩ እኔ በራሴ ቋንቋ ነው የምፀልየው በማለት መልስ ሰጠው::

አቤኔዘር ለጓደኛው እንዲህ አለው አየህ ሰባኪው ያለው ትክክል ነው:: አንተ የተረዳህበት መንገድ ግን ልክ አይደለም:: እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ከአብ የሚወጣው አጽናኝ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይምሰክራል::እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያው ከእኔ ጋር ስለ ነበራችሁ ትመሰክራላችሁ ብሎአል ዮሐ.15፥26-27 በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተሀል በእግዜአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው ጌታን እንደግል አዳኝህ አድርገህ መቀበልህ ቃሉን ማንበብህና በፀሎት ምርት መጠየቅህ በመንፈስ ቅዱስ የመሞላትህ ምልክት ነው:: ተስማምተው ለምስክርነት ወጡ::

ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም በይሁዳ አገር ሁሉ በሰማርያና እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ ሐዋ. 1፥8

የአይሁድ ፋሲካ ባለፈ በሃምሳኛው ቀን በሚከበረው በጴንጤቆስጤ በዓል ደቀመዛሙርቱ ሁሉ በአንድነት በአንድ ቦታ ተሰብስበው ነበር በድንገት ብርቱ አውሎ ንፋስ የመሰለ ድምፅ ከሰማይ መጣ የነበሩበትንም ቤት ሞላው የእሳት ነበልባሎች የሚመስሉም ምላሶች ታዩአቸው ተከፋፍለውም በእያንዳንዳቸው ላይ አረፉባቸው ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ መንፈስ ቅዱስ እንዲናገሩ በሰጣቸው ችሎታ መጠን በሌሎች ቋንቋዎች መናገር ጀመሩ። በዚህ ጊዜ ነው የዮሐንስና የጴጥሮስ አንደበት የተከፈተው ይህን ኃይል ያልተቀበለ በሙስሊም ወንድሞችና እህቶች በሌሎችም ሀይማኖታዊ ድርጅት የሚከተሉ ሰዎች ፊት ቆሞ የጌታ ምስክር መሆን አይችልም ሐዋ. 2፥1-4

ጴጥሮስና ዮሐንስ ለሕዝቡ ሲናገሩ ሳሉ ካህናትና የቤተመቅደሱ የዘበኞቹ አለቃ እንዲሁም ሰዱቃውያን ወደ እነርሱ መጡና ሁለቱ ሐዋርያት የኢየሱስን ከሞት መነሣትና የሙታን ትንሳኤ መኖሩን በማስተማራቸው ተቆጡ። በያዙአቸው ጊዜ መሽቶ ስለነበር እስከ ማግስቱ ድረስ በወህኒ ቤት እንዲቆዩ አደረጉአቸው ነገር ግን ቃላቸውን ከሰሙት ሰዎች ብዙዎች አመኑ የአመኑትም ሰዎች ቁጥር ወደ አምስት ሺ ከፍ አለ።

በዚህም ጊዜ ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንዲህ ሲል መለሰላቸው እናንተ የሕዝብ አለቆችና ሽማግሌዎች ሆይ እኛ ዛሬ የምንጠይቀው ለአንድ ሽባ ሰው ስለተደረገለት መልካም ሥራና በምን አይነት ሁኔታ እንደ ዳነ ነው። ይህ ሰው ድኖ በፊታችሁ የቆመው እናንተ በሰቀላችሁትና እግዚአብሔር ከሞት ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንደሆነ ለእናንተ ለሁላችሁ ለእስራኤል

ሕዝብ ሁሉ የታወቀ ይሁን እናንተ ግንበኞች ንቃችሁ የጣላችሁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ዋና ድንጋይ ሆነ ስለዚህ ደኅንነት ከእርሱ በቀር በሌላ በማንም የለም ምክንያቱም እኛ ልንድንበት የሚገባን እግዚአብሔር የሰጠው ስም ከእርሱ በቀር በመላው ዓለም ማንም የለም።

ከዚህ በኋላ ጠሩአቸውና የኢየሱስን ስም በመጥራት ከቶ እንዳይናገሩ ወይም እንዳያስተምሩ በጥብቅ አዘዙአቸው ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን እንዲህ ሲሉ መለሱላቸው ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ ይልቅ ለእናንተ መታዘዝ በእግዚአብሔር ፊት ተገቢ ነውን? እስቲ እናንተ ራሳችሁ ፍረዱ። እኛስ ያየነውን እና የሰማነውን ከመናገር አንቆጠብም ሐዋ. 4፥1-4፣8-12፣18-20

ሰዱቃውያን ከሞት በኋላ ትንሳኤ የለም ብለው የሚያምኑና የሚያስተምሩ ናቸው ሐዋርያት ኢየሱስ ከሞት ስለ መነሳቱ በማስተማራቸው የሙታን ትንሳኤ መኖሩን በማስረዳታቸውተቆጡ። ከሞት በኋላ ትንሳኤና የዘላለም ሕይወት እንዳለ ለአማኞች ማረጋገጫው የኢየሱስ ከሞት መነሣት ነው። የኢየሱስ በመስቀል ተሰቅሎ መሞቱና ከሞት መነሳቱን የማያምኑ የሐይማኖት ሰዎች ትንሳኤ እንዳለ ምን ማረጋገጫ አላቸው? ክርስቶስ ተሰቅሎ ሞተ ከሞት በሦስተኛው ቀን ተነሣ የሚለውን መስማት የማይፈልጉ ሰዱቃውያን ነበሩ ከመካከላቸው የጌታን ሞትና ትንሳኤ ሰምተው ከሁለት ሺህ ሰዎች በላይ ጌታን አምነው ተቀብለዋል ጴጥሮስ ጌታ እንደሞተ ከሞት እንደተነሳ የአይን ምስክር ነው ።ከሞት ተነስቶ ወደ ሰማይ ካረገ አንድ ወር ከሃያ ቀን ከሆነው በኋላ ነው ይህን የምስክር ቃሉን የሚሰጠው። ለዚህ ነው ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም አንልም ያሉት፣ ጌታን በአይናቸው ስለአዩትና ከአንደበቱ ቃሉን ስለ ሰሙ ነው።

# II. እስልምና

## የእስልምና ሃይማኖት መልእክተኛ የነብዩ መሐመድ ታሪክ

*ሀጂ መሐመድ ሳኒ በፃፉት መጽሐፍ ገጽ 1፣6፣22*

### ከነቢዩ መሀመድ መምጣት በፊት የዐረቦች ሁኔታ

የኢብራሂምና የኢስማኤል ሃይማኖት /በአንድ አምላክ ብቻ ማምለክ/ በዐረቦች ውስጥ በጥንት ጊዜ በሰፊው ተሰራጭቶ ነበር። ከውስጣቸው የሚያድሰው ነብይ ሳይገኝ ብዙ ዘመናትን በማስቆጠሩ የጥንቱ ሃይማኖት ቀስ በቀስ እየተረሳና እየደከመ መሃይምነት እየበዛ ሄደ። በጊዜው መጥፎ ልማዶችና አማልክቶች እየተመሰረቱ ተሰራጩ። በየነገዱ ብዙ አምላኮች ተቋቁመው ይታመንባቸው ጀመር። አድራጊና ፈጣሪ፡ አደህይና አክባሪ አስታማሚና አሻሪ ሺሚና ሻሪ ተደርገው ስለት ይሳሉላቸው ጀመር። ጧት ማታ ይሳለሙዋቸውና ይሰግዱላቸው ጀመር። በዚህ ዓይነት የጥንቱ ሃይማኖት ማለት በአንድ አላህ ብቻ ማምለክ በጭራሽ ተደመሰሰ። ይህ ሁኔታ በብዙ ትውልድ ላይ ተላለፈ።

የተቀደሰው የአላህ ቤት ካዕባን የጣዖታት ማምለኪያ አደረጉት። በውስጡና በዙሪያው 360 ጣዖታት ነበሩ። የነኢብራሂምና የእስማኤል ምስሎች ይገኙባቸው ነበር። ከነርሱም ዋናው ሁበል የሚባለው በካዕባ ውስጥ የነበረው አምላካቸው ነው። ሌሎችም ላትና መናት ዑዛ የሚባሉ የገነኑ አምላኮች ከመካ ውጭ ነበሩአቸው። ፈጣሪን ለቀው ጣዖታት ከማምለካቸው በላይ አንዱ ነገድ ሌላውን በመውጋትና በመዝረፍ ነፍስን በከንቱ በመግደል መጥፎ ሥራ የተባለው ሁሉ በመሥራት የታወቁ አረመኔዎች ነበሩ። የጥንቆላ ሥራ በጣም የተስፋፋና የሚያምኑበት ስለነበረ ብዙ ጠንቋዮች ነበሩባቸው። ይህ ሁሉ መጥፎ ነገር እንዲወገድና ከጨለማ ወደ

ብርሃን እንዲመጡ አላህ ስለ ፈቀደ በውስጣቸው የብርሃን መፈንጠቂያ የሆኑትን ታላቁ ነቢይ መሀመድን አስገኘ::

በ570 ዓመት ልደት በእስያ ክፍለ አህጉር በቀይ ባህር አጠገብ በምትገኘው በስመጥሩይቱና በተቀደሰችው በመካ ከተማ ተወለዱ:: የትውልድ ዘራቸው ከነብዩ ኢብራሂም /አብርሃም/ልጅ ከኢስማኤል ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው በገናናነት ከታወቀው ቁረሽ ከሚባለው ነገድ /ጐሳ/ ነው::

ከኢብራሂም አንስቶ እስከ ነብዩ መሀመድ ሠላሳ ትውልድ አለ:: የስማቸው ዝርዝር ሲረቱ ኢብኒ ሂሻም በተባለው መጽሐፍ ውስጥይገኛል:: አባታቸው አብደላህ እናታቸው አሚናህ ይባላሉ:: አያታቸው አብድልሙጦሊብ ለቁረሾች ታላቅ መሪና ግርማ ያላቸው ተፈሪ ሰው ነበሩ ዐብዱልሙጦሊብን ሃሺም ወለዱ ሃሺምን ዐብዱ:መናፍ ዐብዱ:መናፍን ቁሶይ ወለዱ:: የቁረሽ አስተዳደር መሪነቱ ለየጐሳው ተከፋፍሎ የነበረውን ባድነት ተጠቅልሎ እንዲመራ ያደረጉት ቁሶይ ናቸው :: ቁሰይን ደግሞ ሐኪም /ኪላብ/ ሐኪም ሙራህ ሙራህ ካዑብን ካዕብ ሉአይ ሉአይ ጋሊብ ጋሊብ ፊህር ወለዱ ፊህር በተጨማሪ ቁረሽ ተብለው ይጠሩ ነበርና የሳቸው ትውልድ ሁሉ በዚህ ስም ተጠርቶአል:: ፊህርን ደግሞ ማሊክ ማሊክን ነድር ነድርን ኪናናህ ኪናናህን ኹዘይማን ኹዘይማን ሙድሪካን መድሪካን ኢልያስ ኢልያስን ሙደር ሙደርን ኒዛር ኒዛርን መዐድ መዐድን ዐድናን ወለዱ:: ዐድናን ለነብዩ መሀመድ ሃያ አንደኛ አያት ናቸው:: ከዚህ በላይ ባሉት ባንዳንዶቹ ስም ላይ ታሪክ ጸሐፊዎች ስለሚለያዩባቸው ገድፈነዋል::

የነብዩ መሀመድ አባት ነጋዴ ነበሩ:: የሃያ አራት ዓመት ወጣት ሆነው ሳሉ ልጃገረዲቱን አሚናህ ቢንቱ ወሀብን

አገቡ:: አሚናህ ካገቡ ዓመት ሳይሞላቸው በረጀብ ወር አረገዙ /ፀነሱ/ አንድ ሁለት ወር እንደ ሆናቸው ዐብዱላህ ለንግድ ወደ ሻም /ሶሪያ/ ሄዱ:: ገዛ/ጋዛ/ ደርሰው ሸጠው ለውጠው ሲመለሱ መዲና ሲደርሱ እግረ መንገዳቸውን ዘመዶቻቸውን ለማየት አገለሉ::እዚያም በድንገት ታመው አንድ ወር ያህል ሕመሙ ከቆየባቸው በኋላ ሙሽራይቱን ባለቤታቸውን ሳያዩ እንዲሁም በጉጉት የሚጠባበቁትን ልጅ ተወልዶ ለማየት ሳይበቁ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: አሚናህ እንደዚህ ያለው አሳዛኝ አደጋ ሳይታሰብ ስለ ደረሰባቸው ከመጠን በላይ የሆነ ሀዘን ቢሰማቸውም ባንድ በኩል ደግሞ የተገረዘው ሕፃንና ስለ እርሱ እየተከታተለ ይታያቸው የነበረው ሕልም ተስፋቸውን እያደሰው ሄደ:: ካረገዙ ጊዜ ጀምሮ እስኪወልዱ ድረስ በየወሩ አንዳንድ ነቢይ እነ ነቢይ ኢብራሂም እነ ነብዩ ሙሳ እነ ነቢዩ ኑሕ እነ ነብዩ ኢስማኤል እነ ነብዩ ዒሳ እነ ነብዩ ዳውድ/ዳዊት/ እነ ነብዩ ሱለይማን /ሰለሞን/ ሌሎችም በሕልማቸው እየመጡ ይታዩአቸው ጀመር:: አይዞሽ አትባቢ ባለ እድል ነሽ ይህ ያረገዝሽው ሕፃን የመጨረሻው ታላቅ ነቢይ ነው እያሉ ያጥናኑአቸው ነበር::

ባረገዙ በስድስት ወራቸው መልአኩ ጅብሪል/ገብርኤል/ በህልም ተገልጾላቸው አሚናህ ሆይ የዓለምን ጌታ አርግዘሻልና ደስ ይበልሽ ሲወለድ ስሙን ሙሐመድ ብለሽ ጥሪው ምስጢርሽን ሸሽጊ አላቸው:: በዘመኑ የነበሩ ጠንቋዮችና ኮከብ ቆጣሪዎች የመጨረሻው ነቢይ ኮከቡ ወጥቷል::በዚህ ዘመን ይወለዳል እያሉ ወሬውን በማጋነን አሰራጩት::

ሙሐመድ የተወለዱ ዕለት ብዙ አስደናቂ ነገሮች ሆነዋል:: በተወለዱበት ሰዓት እንደ ፀሐይ ብርሃን ያለ ቀበሌውን አበራው ጮራው እስከ ቡስራ /ሐውረን/ ድረስ ተፈንጥቆ ታየን ሲሉ አዋላጆቹና እናታቸው አረጋግጠዋል :: የፋሪስ ሰዎች በእሳት ያመልኩ ነበርና ሺ ዓመት ያህል እየነደደ ሳይጠፋ የቆየው

የሚያመልኩበት እሳታቸው በዚያ ቀን ያለ አንዳች ምክንያት ጠፍቶ አደረ።

የሀዋዚን ሴቶች ከወላጆች ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ የሚያሳድጉት ልጅ ፍለጋ ወደ መካህ በብዛት መጥተው ነበር። ሐሊማም በጣም ችግር የጠናባት ስለነበረች አብራ መጥታ ነበር። አህያዋ ደካማ ስለነበረች ሌሎቹ ሴቶች ቀድመዋት ሄደው የሀብታሞቹን ልጆች እየተሻሙ ያዙባት። እንደ ደረሰች ብትጠይቅ የሀብታሞቹን ልጆች ተቀድመሻል ። አንድ አባቱ የሞቱበት ሕፃን ብቻ አለልሽ ስለ ተባለች በሱ ሰበብ አላህ ያዝንልኝ ይሆናል ባዶ እጄን ከምመለስ ድሀም ቢሆን እወስደዋለሁ አሳዩኝ አለች ፊቱን ገልጠው ባሳዩዋት ጊዜ በፊቱ የሚፈልቀውን ኑር /ብርሃን / አየችና ልቧ ደነገጠ በፍቅር ተማረከች። ባልዋም ተከትሏት ስለ ነበረ ነገሩን ብታየው ይህ ልጅ ብሩክ ሳይሆን አይቀርምና በሱ ሰበብ አላህ ይረዳናል እንያዘው አላት።

ልጁን ከተቀበሉበት ቀን ጀምሮ ችግር እየለቀቃቸው ምቾት አጥለቀለቃቸው ። አገራቸው እንደ ደረሱ ዝናም ለገሰላቸውና በጣም ጥጋብ ሆነ። ደርቃ የነበረችው ግመላቸውና ፍየሎቻቸው ወተታቸው ተንፏፏ ምቾትና ደስታ ባገሩ ላይ ሰፈነ።

የልጁ መፋፋትና ቶሎ ቶሎ ማደግ ያስደንቅ ነበር። ባንድ ቀን የወር ያህል ባንድ ወር ያመት ያህል ይፋፋ ነበር። ስለዚህ በሶስት ወሩ መቆም ባምስት ወሩ እንደ ልቡ መሄድ ቻለ። በዘጠኝ ወሩ አፍ ፈትቶ አረብኛ በትክክል ተናገረ።

ሙሐመድ ሐሊማ ጋር በነበሩበት ጊዜ ከፍየል እረኞች ጋር አብረው እየሄዱ ግመልና ፍየል ያሰማሩ ነበር። ከእለታት አንድ ቀን ሁለት መልአኮች በሰው ተመስለው መጡና ሙሐመድን ከልጆቹ መካከል ይዘው ጣሉት። ደረቱን በብለዋ ቀደው ልቡን አወጡና

አገቡ። አሚናህ ካገቡ ዓመት ሳይሞላቸው በረጀብ ወር አረገዙ /ፀነሱ/ አንድ ሁለት ወር እንደ ሆናቸው ዐብዱላህ ለንግድ ወደ ሻም /ሶሪያ/ ሄዱ። ገዛ/ጋዛ/ ደርሰው ሸጠው ለውጠው ሲመለሱ መዲና ሲደርሱ እግረ መንገዳቸውን ዘመዶቻቸውን ለማየት አገለሉ።እዚያም በድንገት ታመው አንድ ወር ያህል ሕመሙ ከቆየባቸው በኋላ ሙሽራይቱን ባለቤታቸውን ሳያዩ እንዲሁም በጉጉት የሚጠባበቁትን ልጅ ተወልዶ ለማየት ሳይበቁ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። አሚናህ እንደዚህ ያለው አሳዛኝ አደጋ ሳይታሰብ ስለ ደረሰባቸው ከመጠን በላይ የሆነ ሀዘን ቢሰማቸውም ባንድ በኩል ደግሞ የተገረዘው ሕፃንና ስለ እርሱ እየተከታተለ ይታያቸው የነበረው ሕልም ተስፋቸውን እያደሰው ሄደ። ካረገዙ ጊዜ ጀምሮ እስኪወልዱ ድረስ በየወሩ አንዳንድ ነቢይ እነ ነቢይ ኢብራሂም እነ ነብዩ ሙሳ እነ ነቢዩ ኑሕ እነ ነብዩ ኢስማኤል እነ ነብዩ ዒሳ እነ ነብዩ ዳውድ/ዳዊት/ እነ ነብዩ ሱለይማን /ሰለሞን/ ሌሎችም በሕልማቸው እየመጡ ይታዩአቸው ጀመር። አይዞሽ አትባቢ ባለ እድል ነሽ ይህ ያረገዝሽው ሕፃን የመጨረሻው ታላቅ ነቢይ ነው እያሉ ያጥናኑአቸው ነበር።

ባረገዙ በስድስት ወራቸው መልአኩ ጅብሪል/ገብርኤል/ በህልም ተገልጾላቸው አሚናህ ሆይ የዓለምን ጌታ አርግዘሻልና ደስ ይበልሽ ሲወለድ ስሙን ሙሐመድ ብለሽ ጥሪው ምስጢርሽን ሸሽጊ አላቸው። በዘመኑ የነበሩ ጠንቋዮችና ኮከብ ቆጣሪዎች የመጨረሻው ነቢይ ኮከቡ ወጥቷል።በዚህ ዘመን ይወለዳል እያሉ ወሬውን በማጋነን አሰራጩት።

ሙሐመድ የተወለዱ ዕለት ብዙ አስደናቂ ነገሮች ሆነዋል። በተወለዱበት ሰዓት እንደ ፀሐይ ብርሃን ያለ ቀበሌውን አበራው ጮራው እስከ ቡስራ /ሐውረን/ ድረስ ተፈንጥቆ ታየን ሲሉ አዋላጆቹና እናታቸው አረጋግጠዋል ። የፋሪስ ሰዎች በእሳት ያመልኩ ነበርና ሺ ዓመት ያህል እየነደደ ሳይጠፋ የቆየው

የሚያመልኩበት እሳታቸው በዚያ ቀን ያለ አንዳች ምክንያት ጠፍቶ አደረ::

የሀዋዚን ሴቶች ከወላጆች ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ የሚያሳድጉት ልጅ ፍለጋ ወደ መካህ በብዛት መጥተው ነበር:: ሐሊማም በጣም ችግር የጠናባት ስለነበረች አብራ መጥታ ነበር:: አህያዋ ደካማ ስለነበረች ሌሎቹ ሴቶች ቀድመዋት ሄደው የሀብታሞቹን ልጆች እየተሻሙ ያዙባት:: እንደ ደረሰች ብትጠይቅ የሀብታሞቹን ልጆች ተቀድመሻል :: አንድ አባቱ የሞቱበት ሕፃን ብቻ አለልሽ ስለ ተባለች በሱ ሰበብ አላህ ያዝንልኝ ይሆናል ባዶ እጄን ከምመለስ ድሀም ቢሆን እወሰደዋለሁ አሳዩኝ አለች ፊቱን ገልጠው ባሳዩዋት ጊዜ በፊቱ የሚፈልቀውን ኑር /ብርሃን / አየችና ልቧ ደነገጠ በፍቅር ተማረከች:: ባልዋም ተከትሏት ስለ ነበረ ነገሩን ብታየው ይህ ልጅ ብሩክ ሳይሆን አይቀርምና በሱ ሰበብ አላህ ይረዳናል እንያዘው አላት::

ልጁን ከተቀበሉበት ቀን ጀምሮ ችግር እየለቀቃቸው ምቾት እጥለቀለቃቸው :: አገራቸው እንደ ደረሱ ዝናም ለገሰላቸውና በጣም ጥጋብ ሆነ:: ደርቃ የነበረችው ግመላቸውና ፍየሎቻቸው ወተታቸው ተንቧቧ ምቾትና ደስታ ባገሩ ላይ ሰፈነ::

የልጁ መፋፋትና ቶሎ ቶሎ ማደግ ያስደንቅ ነበር:: ባንድ ቀን የወር ያህል ባንድ ወር ያመት ያህል ይፋፋ ነበር:: ስለዚህ በሰስት ወሩ መቆም ባምስት ወሩ እንደ ልቡ መሄድ ቻለ:: በዘጠኝ ወሩ አፍ ፈትቶ አረብኛ በትክክል ተናገረ::

ሙሐመድ ሐሊማ ጋር በነበሩበት ጊዜ ከፍየል እረኞች ጋር አብረው እየሄዱ ግመልና ፍየል ያሰማሩ ነበር:: ከእለታት አንድ ቀን ሁለት መልአኮች በሰው ተመስለው መጡና ሙሐመድን ከልጆቹ መካከል ይዘው ጣሉት:: ደረቱን በብለዋ ቀደው ልቡን አወጡና

ስነጠቁት:: በብር ሳፋ ላይ አድርገው ከወርቅ ኩሽኩስት የዘምዘም ውሀ እያፈሰሱ አጠቡትና እንደ ነበረ መልሰው በማህተም አተሙበት::

አሚናህ ከዘመድ አስተዋውቋአቸው ሲመለሱ መካ ሳይገቡ በመንገድ ላይ እንዳሉ አብዋእ በሚባል ሥፍራ እንደ ደረሱ በድንገት ታመው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ሙሐመድ ከአባታቸው ቅርስ ያገኘ ዋት አገልጋያቸው ኡመአይመን /በረካ/ አብራቸው ስለነበረች መካህ ወስዳ ለአያታቸው ለዐብዱል መጦሊብ አስረከበች::

ከዚህ በኋላ ለአጐቶቻቸው ለነ አቡ ጧሊብና ለነ ሐምዛ አማክረው በደስታ ስለተስማሙ በ25 ዓመት ዕድሜአቸው ይህችን በእድሜ የምትበልጣቸውን ጭምትና ብልህ ሴት ወ/ሮ ከድጃን አገቡ:: ሲጋቡ ከድጃ ዕድሜአቸው አርባ ዓመት ነበር:: ከተጋቡ ጀመሮ ምንም እንከን ሳይገኝባቸው በስምምነትና በፍቅር በመተባበርና በመከባበር 25 ዓመት አብረው ኑረው ስድስት ልጆች ወልደው ከድጃ በ65 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ::

ነቢዩ መሐመድ ሁለት ወንዶች ልጆች አራት ሴቶች ወልደዋል:: የወንዶቹ ስም የመጀመሪያ ልጃቸው ስም ቃሲም ሁለተኛ ው አብደላህ ናቸው:: ዐብደላህ የተባለው በተጨማሪ ጧሂርና ጦይብ ይባል ነበር:: ሁለቱም በልጅነታቸው ሙተዋል:: የሴቶቹ ስም ዘይነባ ሩቅያ ኡሙ ኩልሱም ፋጢማ ናቸው:: ሴቶቹ ልጆች ትዳር እንደያዙ ሁሉም ሙተዋል የቀረችው ፋጢማ ነች:: እርሷም ለአጐታቸው ልጅ ለአሊ ድረዋት ሐሰንና ሁሴንን ወልዳለች::

ነቢዩ መሀመድ መዲና ከሄዱ በስምንተኛው ዓመታቸው ማሪያ ከሚትባል ግብፃዊት ሴት ኢብራሂም የሚባል ልጅ ወልደዋል እርሱም አንድ ዓመት ተኩል ሲሆነው ሙቶአል::

ከድጃ ከሞተች በኋላ በልዩ ልዩ ምክንያት ሴቶች አግብተዋል ከተከታዮቻቸው ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች እንዳያዝኑ እና እንዳይቸገሩ ልጆቻቸው እንደ አባት ሆኖ ለማሳደግ አግብቶአቸዋል::

በ 610 ዓ.ም. ልክ 40 ዓመታቸው ሂራ በተባለ ዋሻ ሳሉ መልአኩ ጀብሪል መጥቶ አላህ አንተን ነቢይና መልክተኛው እንድትሆን መርጦሀል ከአላህ ዘንድ የሚመጣልህን ቃል በአምላክህ ስም አንብብ ካላቸው ቀን ጀምሮ የነቢይነታቸው ቀን ሆነ።

መሐመድ በመካ የነበረውን ጣኦት በመቃወም አላህ ብቻ ነው እውነተኛ አምላክ በማለት ተቃወማቸው መላእክት፣አጋንንት፣ሰይጣንን ለእነዚህ ሁሉ አምልኮ አይገባቸውም አምልኮ የሚገባው ለአንዱ ለአላህ ብቻ ነው።የመጀመሪያ የእስልምና እምነት ተከታይ ባለቤቱ ከዲጃ ነች። ሁለተኛው የአጐቱ ልጅ አሊ ነው። በጊዜው አጠቃላይ ቁጥራቸው 75 ነበር። ከአፍሪካ የመጀመሪያው የእስልምና እምነት ተከታይ ኢትዮጵያዊው ቢላል ነው ። በመካ ተቃውሞ ስለገጠመው ወደ ያትርብ ተሰደደ ከመካ 280 ማይል ይርቃል። ሐምሌ 16/622 ከመካ ወደ ያትርብ ያደረጉት ጉዞ ሂጅራ ይባላል። የእስላሞች ቀን አቋጣጠር የሚጀመረው ከዚህ ነው በመዲና የተዋጣላቸው ሰው ሆኑ። ብዙ ሰዎች የእስልምና ሀይማኖትን ተቀብለዋል። በ 630 ወደ መካ ተመልሰዋል ወደ መካ ከተመለሱ ከሁለት ዓመት በኋላ በ632 በድንገት ሕይወታቸው አለፈአል።መሀመድ ከሞቱ በኋላ የመሪነቱን ቦታ የተረከቡት ከልፋዎች ናቸው። እስልምና የተስፋፋው በእነዚህ ከልፋዎች አማካይነት ነው። ከልፋ ማለት በአረብኛ ምትክ ማለት ነው።

## 1. የኢማን /የእምነት/ መሰረቶች

*የእምነት ዋና ዋና መሰረቶች ስድስት ናቸው*

ሀ. በአላህ ማመን

ለ. በመላኢኮች /በመላእክት / ማመን

ሐ. በሩሱሎች /በነቢያቶች / ማመን

መ. በኪታቦች /በመጽሐፍት / ማመን

ሠ. በመጨረሻው ቀን ማመን

ረ. በቀደር ማመን ናቸው:: ቀደር ማለት ሁሉን ነገር በአላህ አስቀድሞ የተወሰነ መሆኑን መቀበል ማለት ነው::

### የእስልምና የተግባር መሰረቶች

ሀ. ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም:: ሙሐመድ መልእክተኛው ነው ብሎ በልቦናው አምኖ በምላስ ማረጋገጥና መመስከር ነው ::

ለ. ሦላትን አስተካክሎ መስገድ

ሐ. ዘካን ለሚገባቸው ድኃዎች መስጠት::

መ. የሮመዳንን ወር መፆም

ሠ. ሀጂ ማድረግ ናቸው ::

## 2. በእስልምና ስር ያሉ የእምነት ክፍሎች

በዘመናት ሁሉ እስልምና እየሰፋ በመጣ ቁጥር በመሀከላቸውም ያለው ክፍፍሉም እየበዛ መጥቶአል:: በእስልምና ያለው ጥንካሬ እና አንድነት በቅዱስ ቁርዓን እና በአምስቱ ምሶሶዎች መሰረተ እምነት ያላቸው መታዘዝና መያያዝ ነው:: ከነብዩ መሀመድ ሞት በኋላ በመካከላቸው ልዩነቶች መከሰት የጀመሩት ለዚህ አስተዋፅኦ ያደረገው መሀመድ በከልፋዎች ምስረታ አለመሳተፉ በሕይወት ሳለ የሚተካው ሰው አለማዘጋጀቱ በተጨማሪም አብሮ መታየት ያለበት መሐመድ ወንድ ልጅ አለ መውለዱ መሀመድ በሞተ ጊዜ በመካከላቸው ታላቅ ግራ መጋባት ተከስቶ ነበር::

ሱኒ፡- በሚባለው የእምነት ቅርንጫፍ ከአጠቃላይ የእስልምና እምነት ተከታዮች ከ80-90 ከመቶው ሙስሊሞች የእዚህ እምነት ተከታዮች ናቸው:: ይህ በእስልምናው ዘንድ የኦርቶዶክስ ቅርንጫፍ ይባላል ስሙ የሚያመለክተው የሱኒ የእምነት ተከታዮች በነብዩ ትምህርትና ወግ የሚያተኩሩ መሆናቸው ነው::

ሺያ፡- የነብዩን ትምህርትና ወግ ከእስልምና አባቶች ይልቅ በውል ያስተላለፈው ዓሊ የተባለው የነቢዩ ከልፋ ስለሆነ ራሳቸውን ከሌላው ለየት ባለ መንገድ የእርሱ ማኅበር ነን ብለው ይጠራሉ።

መታዚለተስ፡- የሚባለው የእስልምና እምነት ቅርንጫፍ በ732 ዓ.ም. ተመሰረተ የቁርአን ዘላለማዊነትን ይቃወማሉ ቁርዓን ከጊዜ በኋላ የመጣ እንጂ ከጥንት የነበረ ወይም ዘላለማዊ አይደለም ይላሉ። ባሕላዊውን ከአላህ ለሰዎች ተሰጠ ተብሎ የሚታመነውን የሥልጣን ተዋርድ አይቀበሉም ። አላህ የከፋ ነገር ሁሉ ምክንያት ነው ይላሉ።

በአንፃሩ ሰው ነፃ የሆነ ፈቃድ አለው። የእነርሱ እምነት ተከታይ መጥፎና መፈፀም የሌለበተ ኃጢአት ሰርቶ ቢሞት ያ ግለሰብ ጠፍቶአል። በእነርሱ አመለካከት ሐይማኖት የሰው ልጅ ሕይወቱን የሚንከባከብበት ድርጅት ነው።

ዋሀቢያ፡-/ORTHODOX ISLAM/

አብድል ወሀብ 1691ዓ.ም. ተወለደ አብድል ወሀብ ትጉና የቁርዓንን ትምህርት ጠንቅቆ የተማረ ሰው ነበር። አላማው በእስልምናው ዓለም ተሀድሶ ለማምጣት ነው። ለወደፊት ሊሆን ያለውን ማወቅ ወይም ትንቢትን ይቃወማል። ጥንቆላ ዲቤ መምታት ለሰው የሚደረግ አምልኮ ይቃወማል። ቅዱስ ቦታዎች ተሂዶ መቃብር፣መሳለም ሰው ከሞተ በኋላ ግለሰቡን ወደ ገነት ለማስገባት የሚደረገውን ሥርዓት ይቃወማል። ሰው የሕይወቱን አቅጣጫ ማስተካከል የሚችለው በሕይወት ሳለ እንጂ። ከሞት በኋላ ሰደቃ ቢደረግለትም ምንም አይጠቅመውም። መጠጥ መጠጣትን ማጨስን ይከለክላሉ። ጥረታቸውን የመጀመሪያው የእስልምና ይዘትና እንቅስቃሴ ለመመለስ ነው። ብዙ ተከታዮችን አፍርቶአል ቢሆንም በጊዜው በነበሩት ገዢዎች ተቃውሞ ገጥሞታል። በዚህ ጊዜ

መሀመድ ኢቢን በይድ መጠጊያ እንደ ሚሰጠው ተስፋ ሰጥቶት ነበር ተልኮውን ሳይፈፅም ሕይወቱ አልፎአል ::

አህመድያን :-

የዚህ ጉሩፕ መስራች ማርዛ ገለም አሕመድ ይባላል:: የኖረበት ዘመን እ.አ.አ ከ1865-1908 ሲሆን የተመሰረተው በህንድ ነው:: ራሱን ነብይ ብሎ ጠርቶአል:: የኢየሱስ ክርስቶስ ተዓምራቶችንና ወደ ምድር መጥቶ የሰራውን ሥራ ሁሉ ይቃወማሉ:: ቁርዓን የክርስቶስን መስቀል ይቃወማል አህመድያን ግን በመስቀል ላይ መሰቀሉ ተሰቅሎአል:: ሳይሞት በሕይወት ሳለ ወርዶ ወደ ካሽማር ሸሽቶአል ቀሪ የሕይወት ዘመኑ በካሽሚር ኑሮ አርጅቶ ሙቶአል ብለው ያምናሉ:: መቃብሩ እስከአሁን እንዳለ ይናገራሉ::

አህመድ ይጠበቅ የነበረው መሲህ እኔ ነኝ ይላል ይመጣል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው ክርስቶስ ራሱ እንደሆነ ይናገር ነበር:: የእርሱ ተከታዮች ከልፋ ብለው ይጠሩታል ሀይማኖታቸውን ለማሰፋፋት የሚሽነሪይ አገልግሎትን በሰፊው ይሰጣሉ ዘመናዊ ትምህርትንና ዓለም የደረሰችበት ሥልጣኔ ተጠቃሚ ለመሆን ልባቸው ክፍት ነው::አዲስ ነገር ለማወቅ የተዘጋጁ ናቸው::

ባቢዝም :-

መስራቹ ማርዛ አሊ መሀመድ ይባላል እ.አ.አ ከ1821-1850 ዓ.ም. ድረስ ኑሮአል የሺያ እምነት ተከታይ ነበር የተነሣው ከኢራን ነው:: ራሱን በር ብሎ ይጠራል መጽሐፋአቸው ባያነ ተብሎ ይጠራል በመጽሐፉ ውስጥ ያለው ሀሳብ እርሱ ያየው ራዕይ ወይም መገለጥ ይዞአል::

ለራሱ የተለያዩ ስሞችን ሰይሞአል:: ነፀብራቅ እና የእግዚአብሔር ዳግም ልደት በግልጥ እኔ ክርስቶስ ነኝ ብሎ ያውጅ ነበር ትምህርቱ የሚያተኩረው በሥነ ምግባር ላይ ነው::ስህተት

መስራቱን የተገነዘቡ ተከታዮቹ እርሱን እና ትምህርቱን ከመከተል ተመልሰዋል::

ባሀይ:-

ባሀይ:- መስራቹ ባቢ ማርዛ ሆሴን አሊ ኑር ይባላል:: ከ1817-1892 ዓ.ም. የኖረበት ዘመን ሲሆን የተነሣው ከኢራን ነው እንደ ሌሎቹ የሀይማኖት መሪዎች ለራሱ ስም አውጥቶአል ራሱን የእግዚአብሔር ብርሀን ብሎ ጠርቶአል:: መጽሐፉም ኪታብአል አኪዳስ ይባላል:: በተጨማሪ ከእግዚአብሔር የወጣ ጨረር የሚል ስያሜ አለው የእርሱ እምነት በሚመጡት ዘመናት ዓለም አቀፋዊ ሐይማኖት እንደሚሆን ይናገራሉ ፍቅርን ለሰው ሁሉ ማሳየት መልካም ሥራ መስራት የወደፊት አላማቸው አንድ ዓለም አቀፍ ቋንቋና ሐይማኖት መመስረት ነው:: ወደ ፊት በዓለም ላይ አንድ ሀይማኖት ብቻ ይኖራል እርሱም ባሀይ ነው::

ሱፊዝም ሳፊዎች/ Fock Islam /

ሱፉዝም የሚለው ቃል የመጣው ሳፍ ምናልባትም ሳፋ የቃሉ ትርጉም ንፁህ ማለት ነው:: ምናልባትም ሶፍያ ትርጉሙ ጥበብ ማለት ነው:: ሱፋ ከአረብ ዝርያዎች መካከል በመካ መሰግድ ውስጥ የሚያገለግሉ ናቸው::

እነዚህም እንደ ሌሎች እስላሞች ፈጣሪ ሩቅ ሆኖ መመሪያ የሚልክ ሳይሆን ልንቀርበው እንድያውም የእርሱን ተፈጥሮ ውስጥ ልንገባ እንችላለን የሚሉ ናቸው:: ለስሜታዊ ልምምድ ያደላሉ፣ ምናኔ የልዩ ልዩ ቦታ ጉዞ፣ፀሎት፣ዝማሬ የቁርዓን ጥቅሶችን መዘመር በተመስጦ ዜማዊ ፀሎት ላይ ያተኩራሉ ታላቅ የበረከት ረሀብ አላቸው :: ከአንድ ልምምድ ወደ ሌላው እየተሻገርን በመጨረሻው በአምላክ እልውና እንሰምጣለን ይላሉ:: የተሳካላቸውን ሰዎች በራማ ይማፀናሉ ::

## ልምምዳቸው በደረጃ ሲቀመጥ

1. ጥሩ እንግዳ ተቀባይነት፣ ሌላውን ማገልገል::
2. ግላዊ ፍቅር ለፈጣሪ፣ ዜማ መጻፍ ፣በሰዎች ፊት በዜማ ማመስገን
3. በልዩ መነቃቃት ውስጥ መግባት ከአካባቢ ሁኔታ መለየትና ልዩ የብቸኘነት የተመሰጠ ጊዜ ማሳለፍ::
4. ስለ ፈጣሪ በሆነ ነገር ላይ ልዩ ልዩ ዕውቀት ውስጥ መግባት
5. ልዩ ልዩ ልምምዶችን መለማመድ ራዕይንና ህልም ማየት
6. እውነትን በመረዳት ልዩ የሆነ ሰማያዊ መገለጥን ማግኘት ፈጣሪን ማወቅ ::
7. በፈጣሪ ህልውና ውስጥ በመስመጥ ከሰውነት ወጥቶ ፍፁም ከሆነ ፈጣሪ ጋር መዋሐድ ናቸው::

### 3. ቁርዓን

የቃሉ ትርጉም ኢቅራ ማለት አንብብ ሲሆን፣እንደ ሙስሊሞች አባባል የሰው ጣት ጣልቃ ሳይገባበት በቀጥታ ከሰማይ የወረደ የሰው የሆነ አንዳች ነገር የሌለበት መለኮታዊ ቃል ነው ይላሉ::

አላህ በመልእክተኛው በጅብሪል /ገብርኤል/ አማካይነት ማንበብ ለማይችሉ ነቢይ በቃሉ እንዲይዘው የገለጠለት መጽሐፍ ነው ይላሉ:: መሐመድ የአላህን መልእክት ለማስተላለፍ የተመረጠ እቃ እንጂ የመልእክቱ አመንጭ አይደለም የመልክቱ ባለቤት አንድ አላህ ነው ይላሉ:: ይህ መጽሐፍ እስላሞች ሊያነቡት፣ ሊፀልዩት፣ ሊያሰላስሉት ግዴታ አለባቸው:: የእስልምና እምነት መካከለኛው እውነት ቁርዓን ነው ይላሉ::

ይዘቱ በአጠቃላይ 114 ምዕራፎች አሉት:: 86ቱ ምዕራፎች ለነቢዩ በመካ በነበሩበት ጊዜ የተገለጠላቸው ሲሆን 26 ደግሞ በመዲና ነው::

አቀማመጡን በተመለከተ ብዙ ቁጥሮች ያሉት ምዕራፎች በመጀመሪያ ሲሆን ሌሎቹ በዚሁ ቅደም ተከተል ተቀናጅተዋል:: (መጽሐፉን በአንድ ላይ ያሰባሰቡት ኡስማን የተባለው ሦስተኛው ከሊፋ ነው:: ጊዜውም ከ644-656 ነው::

ሐዲስ:-የቃሉ ትርጉም አባባል አነጋገር ማለት ሲሆን በተለይም የነቢዩን ንግግር ይመለከታል:: እስልምናን ለመገንዘብ ከሁለት አቅጣጫ ሁኔታዎችን ማየት ያስፈልጋል:: የመጀመሪያው ቁርዓን ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ሐዲስና ሱና ተብለው ይጠራሉ:: ሱና የነብዩ ልማድና ወግ ተግባራዊ ልምምድ ማለት ነው:: እስልምና ከሐዲስና ከሱና ውጭ ለመገንዘብ በጣም አዳጋች ነው::

## 4. የእስልምና ግንዛቤ

### *ሀ. ስለሰው*

በእስልምና ፈጣሪ ሰውን ከምድር አፈር እንዳበጀው ይታመናል::ሱራቱል ሃጅር 15:26-28 ስለ አፈጣጠሩ ዝርዝር ማብራሪያ አሰጣጥ ላይ ከክርስትና ይለያል ይህ የተፈጠረው ሰው ልዩ የአምላክ ሥራ አመልካች ዕፁብ ድንቅ የፈጣሪ ሥራ መሆኑን በማስገንዘብ ፈጣሪ ለሰው እንዲሰግዱ ቢጠይቅ ኢብሊስ /ከመላዕክት አንዱ/በኩራት እምቢ በማለቱ በፈጣሪ ተረገመ ከዚህ የተነሣ በሰው የበቀልን እርምጃ ወስዶ ሰውን አትቅረብ አትብላ የተባለውን ዛፍ እንዲበላ በማድረግ አሳሳተው ይላሉ::

አዳምንም ስሞችን ሁሏንም አስተማረው ከዚያ በመላእከት ላይ /ተጠሪዎቹን/ አቀረባቸው እውነተኞችም እንደሆናችሁ የነዚህን/ተጠሪዎች/ ስሞች ንገሩኝ አላቸው::ሱረቱል በትራ 31-34 ጥራት ይገባህ ከአስተማርከን ነገር በስተቀር ለኛ ዕውቀት የለንም አንተ አዋቂው ጥበበኛው አንተ ብቻ ነህና አሉ::

አዳም ሆይ ስሞቻቸውን ንገራቸው አለው ስሞቻቸውን በነገራቸው ጊዜ እኔ የሰማያትና የምድርን ሩቅ ምስጢር አውቃለሁ የምትገልጹትንና ያንንም የምትደብቁትን የነበራችሁትን አውቃለሁ አላልኳችሁምን? አላቸው ለመላእክት ለአዳም ስገዱ ባልን ጊዜ /አስታውስ/ ሁሉም ወዲያወኑ ሰገዱ አብሊስ /ዲያብሎስ/ ብቻ ሲቀር እምቢ አለ ኮራም ከካሐዲዎችም ኾኑ:: ሱራ 2:31-34

አዳም ሆይ! አንተ ከነሚስትህ በገነት ተቀመጥ ከርሷም ከፈለጋችሁት ስፍራ በሰፊው ተመገቡ ግን ይህችን ዛፍ አትቅረቡ ከበደለኞች ትኾናላችሁና አልንም ከርሷም ሰይጣን አንዳለጣቸው በውስጡም ከነበሩት ድሎት አወጣቸው ከፊላችሁም ለከፊሉ ጠላት ሲኾን ውረዱ ለእናንተም በምድር ላይ እስከ ጊዜ ሞታችሁ ድረስ መርጊያና መጠቀሚያ አላችሁ አልናቸው:: ሱራ 2፥35-36 የሰው አወዳደቅ በቁርዓን በዚህ መልኩ ተገልፆል የወደቁበት ምክንያት ደግሞ እንደሚከተለው ነው::

ለመላእክት ለአዳም ስገዱ ባልናቸው ጊዜ /አስታውስ/ ወዲያውም ሰገዱ ኢብሊስ ብቻ ሲቀር ከጭቃ ለፈጠርከው ሰው እሰግዳለሁ? አለ:: ንገረኝ ይህ ያ በኔ ላይ ያበለጥከው ነውን እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ ብታቆዩኝ ዘሮቹን ጥቂቶች ሲቀሩ ወደ ስሕተት በእግጥ እስባቸዋለሁ አለ::/አላህም/ አለው ኺድ ከነርሱም የተከተለህ ገሀነም የተሟላች ቅጣት ስትኾን ፍዳችሁ ናት::

ከነሱ የቻልከውንም ሰው በድምጽህ አታል በነሱም ላይ በፈረሰኞችህ በእግረኞችህ ኾነህ በገንዘባቸውም በልጆቻቸውም ተጋራቸው ተስፋ ቃልም ግባላቸው ሰይጣንም ማታለልን እንጂ ተስፋ ቃልን አይገባላቸውም :: ሱራ 17፥61-64

ሰው በወደቀ ጊዜ ተጣለ የኃጢአት ባሕርይ በውስጡ ቀረ የሚለውን አስተምሮ አጥብቀው ይቃወማሉ:: ሰው ስለ በደለ ለቅጣት ከሰማይ ገነት ወደ ምድር ተጥሎአል ይህ ደግሞ በሰው ሃይለኛ

ፀፀትን ስለ አሳደረበት በንስሐ ወደ ፈጣሪው ተመልሶ በደሉ ይቅር ተብሉአል። ስለሆነ አዳም ለሰው ልጅ የመጀመሪያው ነብይ መመሪያ ተቀባይ አስተማሪ ሆኖ አገልግሏል።

ስለዚህ የአዳም ኃጢአት ለእርሱ ብቻ ተወስኖ የቀረ እንጂ በዘር የሚተላለፍ አይደለም። እንደ እነርሱ አገላለፅ ሰው ሲወለድ ለክፋም ሆነ ለበጐ የሚመቸውን ምርጫ ይዞ ይወለዳል የሰው ማንነት የሚወሰነው እያደር በሚሠራው ሥራ እንጂ የራሱን እጣ በምድር የኖረው ሰው በእርሱ ሥር የሚመጣውን ሊወስንለት በፍፁም አይችልም። ስለዚህም ክፉ ለመሆን የመረጠ ክፉ፣ደግ ለመሆን የመረጠ ደግ ይሆናል እንጂ ሰውን ወደ ክፋ የሚመራ በሰው ውስጥ በአመዛኙ በክፋ ያደላ ማንነት በጭራሽ የለም ብለው ይሟገታሉ።

ባጠቃላይ ሰው መልካም የሆነውን ነገር ማስተላለፍ ከቻለ አላህ በሰጠው መመሪያና አስተምህሮ ፍፁም ሆነ መኖር ይቻለዋል። በእርግጥ በሰው ዘንድ ፍፁምነት የለም።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን ፅድቅ ተብሎ የሚታሰበው የሰው ነገር እንኳን የመርገም ጨርቅ መሆኑን የወደቀው ሰው ማንነት ሙሉ የሆነውን የመለኮት ረድኤት ካልተቀበለ ጐዶሎ መሆኑን በጥብቅ ያስተምራል።

አሁን ግን እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያፀድቅበት መንገድ ከሕግ ነፃ ሆኖ ተገልጦአል ይህም በሙሴ ሕግና በነቢያት ተመስክሮአል ስለዚህ እግዚአብሔር ምንም ልዩነት ሳያደርግ በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ ጽድቅን ይሰጣል። ምክንያቱም ሰዎች ሁሉ ኃጢያት ሰርተዋል። እግዚአብሔር የሰጣቸውን ክብር አጥተዋል። ስለዚህ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ በፈፀመው በአዳኝነት ሥራ በእግዚአብሔር ፀጋ ብቻ ይፀድቃሉ። ሮሜ 3፥23-24

በአንድ ሰው ምክንያት ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ በኃጢያት ምክንያት ሞት መጣ:: ይኸውም ሰው ሁሉ ኃጢአት ስለሠራ ሞት በሰው ሁሉ ላይ መጣ ምክንያቱም የሙሴ ሕግ ከመሰጠቱ በፊት ኃጢአት በዓለም ነበር::ይሁን እንጂ ሕግ በሌለበት ኃጢአት እንደ ኃጢያት አይቆጠርም:: ሆኖም እንደ አዳም ሕግን በመተላለፍ ኃጢያት ባልሰሩት ላይ እንኳን ሳይቀር ሞት ከአዳም አንስቶ እስከ ሙሴ በሰው ሁሉ ላይ ሥልጣን አገኘ:: ይህም አዳም ወደፊት ለሚመጣው ክርስቶስ ምሳሌ ነበረ፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር ፀጋ ከሰው ኃጢአት ይበልጣል::በአንድ ሰው ኃጢአት ምክንያት ብዙዎች እንደ ሞቱ እንዲሁም በእግዚአብሔር ፀጋና በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ ምክንያት የተገኘው ስጦታ ለብዙዎች በይበልጥ ተሰጥቶአል:: እንዲሁም የእግዚአብሔር ፀጋ ውጤት ከሰው ኃጢያት ውጤት ይበልጣል:: በአንድ ኃጢያት ምክንያት የተሰጠው ፍርድ ቅጣትን አመጣ በብዙ ኃጢያት ምክንያት የተሰጠው ጸጋን ጽድቅን አመጣ:: በአንድ ሰው ኃጢአት ምክንያት ሞት በሰው ላይ ሥልጣን አገኘ:: በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የእግዚብሔርን ብዙ ፀጋ ተቀብለው የጸደቁ ሁሉ በድል አድራጊነት ሕይወት ይኖራሉ:: ሮሜ 5፥12-17

## ለ. <u>ስለ ኃጢአት</u>

በእስልምና አተረጓጐም ብዙ አባባሎች ያሉት ቢሆንም ክርስቲያኖች ለኃጢአት ካላቸው ግንዛቤ ጋር ፍፁም ይለያያል:: የእስልምና መረዳት ኃጢአት ማለት በእስልምናው አተረጓጐም ወንጀል ከንቱ ድርጊት ከባድ ሽክም፣ መቅበዝበዝ ፣ መጥፋት ፣ ክህደት፣ክፋ ዕጣ፣ውሸት፣ ባጠቃላይ በእስልምና የኃጢአት መግለጫው ድርጊት ብቻ ሆኖ ነው የሚታሰበው:: ስለዚህ መፍትሔው ከግንዛቤው ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው::በእነርሱ መረዳት ከኃጢአት ነፃ የሚያወጣው መፍትሔ ከኃጢአተኛ ኑሮ ለመላቀቅ

አይነተኛው መንገድ የህይወት መመሪያ አላቸው:: በዚህ የሕይወት መመሪያ ውስጥ ሰው ሳይደናቀፍ እንዲኖር የሚደግፍ መምህር ነው ደላሉ:: አስተማሪንና ፍፁሙን ህግ የሚሰማ ሰው ሁሉ እንከን የለሽ ይሆናል ኃጢአትም ኃይል አጥቶ ይሄዳል የሚል እምነት አላቸው::

በእነርሱ አመለካከት የሰውን ብቃት ስለሚያጉሉ በሰውና በአላህ መካከል የኢየሱስ አማላጅነት አስፈላጊ አይደለም በማለት የክርስቲያኖች የኃጢአት ሥርየት ግንዛቤ ይቃወማሉ:: ሰውንና ፈጣሪን ያራራቀ በሰውና በፈጣሪ መካከል ያለ ትልቅ ገደል መኖሩ ቢታመንም ለዚህ ድልድዩ፣ ወይም አሸጋጋሪው መሰላል ለማግኘት አላህን መታዘዝና በፈቃዱ ለመኖር መታገል እንጂ በፈጣሪ እና በፍጡር መካከል የሚገባ ሰው /አዳኝ/ አያስፈልግም ይላሉ:: በእነርሱም ግንዛቤ ከአምላክ ምህረትና ችሎታ ይልቅ የሰውን ብቃትና ችሎታ በአያሌው ያስተጋባሉ::

ክርስቲያኖች ከእስላሞች ጋር በኃጢአት አጀማመር ላይ ቢስማሙም ሰው ከሰይጣን ጋር ለማበር ከፈቀደ፣ እና ከወደቀ በኋላ ማለትም ነፃ ምርጫውን /ነፃነቱን/ ለተሣሣተ ድርጊት ሲጠቀም፣ በዚህ የሰው ልጅ የመጀመሪያ የፈፀመው በደል የተሰጠውን ውክልና አጥቶአል:: ኩነኔም ወደ ሰው በሙሉ በመምጣቱ ሰው በሙሉ ሲወለድ ኃጢአተኛ ሆኖ እንደሚወለድ ያምናሉ:: ኃጢአት ድርጊት ብቻ ሳይሆን በሰው ማንነት ውስጥ የሰለጠነ ገዢ ሀይል ነው:: ስለዚህም ከዘር ወደ ዘር ሊተላለፍ የሚችል በጣም ሥር የሰደደ በአንድ ሰው አመጽ ተከስቶ የሰውን ንፁህ ተፈጥሮ አበላሽቶ በሰው ውስጥ የነገሰ በሰው ያደረ ኃይል ነው:: ከእንዲህ ዓይነቱ ሀይል የሚያስጥል የሰው ሞራላዊ ትምህርት ሳይሆን የአምላክ የታዳጊነት እርምጃ ነው:: ይህ ኃይል ህፃን ቢሆን ወጣት፣ አዋቂ ቢሆን ሽማግሌ በእያንዳንዱ የሰው ዘር ሁሉ ላይ ነግሦአል::

ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ ያለው አላህ ፈቃዱን ለክፉ ያስገዛውን ሰው በሞት ባርነት እንዲቆይና ሞትን እንዲያይ ፈቀደ ከዚህ የተነሣ በኃጢያት በኩል ሞት በሰው ልጅ ነገሰ:: ከዚህ ንጉሥ ተፅኖ ሥር የወደቀውን በፈቃዱ ሰይጣንን ያገለገለው የሰው ልጅ ከሠራው ኃጢአት የተነሣ ከኃጢአት ጋር ምንም ህብረት የሌለው ፈጣሪ ኃጢአትን/ኃጢአተኛውን በኃጢአቱ / መቀጣት የግድ ነበረበት ያለውን የሚፈፅም አላህ ሰውን ከሰይጣን ጋራ ለጊዜው ተወው::

የሰይጣን ምክር በመስማት እጅግ አሣዛኝ አወዳደቅ ለወደቀው ሰው ሰይጣን ነፍስ ገዳይ እንጂ ሌላ ሊሆን ስለማይችል ርህሩህና አዛኝ የሆነው ፈጣሪ የልጅነት መብቱን ያጣውን ሰው እንዲህ ባለ ሁኔታ ሊተወው ስላልወደደ ተስፋን ሰጠ:: ተስፋውም ለዘመናት ሲጠበቅ ቆይቶ በዘመኑ ፍፃሜ አማኑኤል እግዚአብሔር ሰው ሆኖ መጣ:: የሰውን ልጅ ለማዳን::

የሰው ኃጢአት ትምህርትና መመሪያ የሚያስጥለው ምክርና ሕግ የሚያስወግደው ባለመሆኑ አላህ የራሱን መፍትሔ በማዘጋጀት የራሱን ፅድቅ ክርስቶስን በመስጠት ኃጢአተኛውን በምህረቱ ታረቀው::ለምን ቢባል ፅድቅ ተብሎ የሚቆጠረው የሰው ድርጊት እንደ መርገም ጨርቅ ነው:: ኢሳ. 64፥6

እርሱም በዓለም ነበረ ዓለምም የተፈጠረው በእርሱ ነው ዓለም ግን አላወቀውም:: ወደ ገዛ ዘመዶቹ መጣ/ወደ አይሁዳውያን / ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም:: ይሁን እንጂ ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑ የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው ::ዮሐ.1፥10-12

## 5. በእስልምና መንግስተ ሰማያት ለመግባት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች እና ስለመጨረሻው ዘመን

በዓለም ያሉ አብዛኞቹ ሀይማኖቶች መንግስተ ሰማያት ለመግባት አማኞች መተግበር ያለባቸው ቅደም ተከተል አላቸው::

### ሀ. ስለ ደህንነት

**1. *መልካም ሥራ መስራት***

እነዚህ የጌታቸውን ውዴታ ለመፈለግ የታገሱ ሰላትንም አዘውትረው የሰገዱ እኛ ከሰጠናቸው ሲሳይ በምሥጢርም ኾነ በግልፅ የመፀወቱ ክፋውን ነገር በበጉ የሚገፈትሩ ናቸው:: እነዚያ ለእነርሱ መጨረሻይቱ ምስጉን አገር አለቻቸው :: /እርሷም/ የመኖሪያ ገነቶች ናት ይገቡባታል ከአባቶቻቸውም ከሚስቶቻቸውም ከዝርያቸውም መልካም የሰራ ሰው / ይገቡባታል/ መላእክትም በነርሱ ላይ ከየደጃፉ ሁሉ ይገባሉ አልረዕድ 13:22-23

**2. *መፃምና መፅዋት መስጠት***

ሙስልሞች ወንዶችና ሙስሊሞች ሴቶች ምእመናንና ምእመናትም ታዛዦች ወንዶችና ታዛዦች ሴቶች እውነተኞች ወንዶች እውነተኞች ሴቶችም ታጋሾች ወንዶችና ታጋሾች ሴቶችም አላህን ፈሪዎች ወንዶችና አላህን ፈሪዎች ሴቶች መጽዋቶች ወንዶችና መጽዋቾች ሴቶችም ጿሚዎች ወንዶችና ጿሚዎች ሴቶች ካልተፈቀደ ሥራ ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች ወንዶችና ጠባቂዎች ሴቶችም አላህን በብዙ አውሺዎች ሴቶችም አላህ ለእነርሱ ምህረትና ታላቅና ምንዳ አዘጋጅቶላቸዋል:: አልአህዛብ 33:35

3. *ልጆች ከወላጆቻቸው በፊት ቢሞቱ መንግስተ ሰማያት ይገባሉ*

ይህ የሀዲስ አባባል ነው:: በአንዳንድ አካባቢ መንግሥስተ ሰማያት በቤተሰብ የሥልጣን ተዋረደ እንደሚገባ ይታመናል:: በእስልምና ቤተሰብ ትልቅ ቦታ አለው እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የመጣበትን የትውልድ ሀረግ የማወቅ ሀላፊነት አለበት:: በእንዲህ አይነት ህብረተሰብ ወንጌልን ለመስበክ እነርሱን ማድመጥ የአካባቢው ህብረተሰብ ትልቅ ቦታ የሰጠውን የሃይማኖት መሪ አንተ ወይም እርሱ ብሎ አለመጥራት የአካባቢው ሰው የሚጠቀመውን ቋንቋ መጠቀም በአለባበስና በአበላል ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው::

4. *ሃጂ*:-

አቅም በፈቀደ መጠን በህይወት ሳሉ አንድ ጊዜ ወደ መካ የሚደረግ ጉዞ ነው::

ሰፋና መርዋ ከአላህ ትእዛዝ መፈጸሚያ ምልክቶች ናቸው ቤቱን /ከዕባን/ በሐጅ ወይም በዑምሪህ ሥፍራ የጐበኘ ሰው በሁለቱ መካከል በመመላለሱ በርሱ ላይ ኃጢአት የለበትም መልካምን ሥራ በፈቃደኝነተ የሰራ ሰው አላህ ይመነዳዋል አላህ አመስጋኝ አዋቂነውና:: ሱራ2፡158

5. *ደህን መመገብ*

አላህ በመሐላዎቻችሁ ቢወድቁ አይዛችሁም ግን መሐላዎችን ባሳባችሁት ይይዛችኋል ማስተሰሪያውም /ባፈረሳችሁት ጊዜ / ቤተሰቦቻችሁን ከምትመግቡት ከመካከለኛው /ምግብ/ ዐሥር ምስኪኖች ማብላት ወይም ጫንቃን ነፃ ማውጣት ነው:: /ከተባሉት አንዱን/ ያላገኘም

ሰው ሦስት ቀኖችን መጾም ነው:: ይህ በማላችሁ ጊዜ የመሐሉቻችሁ ማስተሰሪያ ነው መሐሉቻችሁን ጠብቁ እንደዚሁ አላህ ለእናንተ አንቀጾችን ያብራራል እናንተ ልታመሰግኑ ይከጀላልና :: ሱራ 5፥89

በሳምንቱ ወይም በቀናቱ መጨረሻ ቀንና ሌሊት መፀለይ ሃጢያትን ያስተሰርያል:: ሰላትንም በቀን መጨረሻ ከሌሊትም ክፍሉች ፈጽም መልካም ሥራዎች ሃጢአቶችን ያስወግዳሉና::ይህ ለተገሣጮች ግሣጼ ነው:: ሱራ 11፥114 ሙስሊሞች የፅድቅ ሥራንና ቅድስና በሕህወታቸው ማየት ይፈልጋሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ ትቀደሱ ዘንድ ፈልጉ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና:: ዕብ. 12፥4
ሙስልም ወንዶችና እህቶቻችን በራሳቸው ጥረትና መልካም ሥራ በመስራት ለሙሴ የተሰጠውን የኦሪት ህግ በመፈፀም መንግስተ ሰማይ ለመግባት ይጥራሉ::

ፅድቅ ለተራበው ሙስልም ህብረተሰብ ወንጌልን መስበክ የዛሬ እና የነገ የቤት ሥራችን ነው:: ከምንናገረው የበለጠ እንደ እግዚአብሔር ቃል እየኖርን እውነትን እናሳያቸው የሰላም ወንጌል እየሰበክን እርስ በእርስ እና ከህብረተሰቡ ጋር በሰላም መኖር ካልቻልን ከእኛ ምን ይማራሉ ወደ እኛስ እንዴት ይመጣሉ::

አንዳንድ ክርስቲያኖች እርስ በእርስ ሲወያዩ ወደ ሙስሊሞች ለምን እንሄዳለን እኛ የራሳችን አለን:: እነርሱም የራሳቸውን አላቸው ይላሉ:: ይህ ማለት ጌታ ያዘዘውን ትዕዛዝ አልፈፅምም ብሎ እምቢይተኛ መሆን ነው:: «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ሥበኩ» :: እነዚህ ወገኖቻችን በተመለከተ ጌታ እንዲህ ብሎአል በዚህ መንጋ ውስጥ ያልሆኑ ሌሎች በጐች አሉኝ::

እነርሱን ማምጣት ይገባኛል እነርሱ ድምፄን ይሰማሉ አንድ መንጋ ይሆናሉ እረኛውም አንድ ይሆናል ዩሐ. 10፥6 እነዚህን በጐች የጌታን ድምፅ አሰምቶ ወደ መንጋው የሚያመጣቸው ማን ነው? ይህ ሥራ በእኔ እና በአንተ በኩል ይከናወናል፡፡

በእስልምና ያለው የሃይማኖት ሥርዓት ማራኪ ነው ለውጫዊ ሥርዓት ያላቸው መታዘዝ መልካም ነው ቢሆንም ያ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ዒሳ እንዲህ ብሎአል መንገድ እውነት ህይወት እኔ ነኝ በእኔ በኩል በቀር ማንም ወደ አብ የሚመጣ የለም ዮሐ. 14፥6 የሰው ሕይወት በፍለጋ የተሞላ ነው የሰው መንፈስ ደግሞ ብርሃንን ፍለጋ ይህን የተረዳው ኢዮብ እንዲህ አለ ወደ ብርሀን መኖሪያ የሚያደርሰው መንገድ የትኛው ነው?ኢዮ. 38፥19

## ለ. ምፀአቱ ወይም ስለ መጨረሻው ቀን ያላቸው አመለካከት፡፡

የዓለም መጨረሻ የሀሰተኛው ክርስቶስ መገለጥና የክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት፡፡ /አቂራ/ ጀማሬና እድገት እንዳለ ሁሉ ፍፃሜ እንደሚኖር ሙስሊሞች ያምናሉ፡፡

ምልክቶቹ

- እስላሞችን እንደ ትልቅ ሕዝብ የሚያደርገው የታላቁ ታዳጊ መሀዲ መገለጥ ለመጨረሻው ቀን ምልክቶች አንዱና ዋናው ነው፡፡
- ከኢራን፣ ከኢራቅ ወይም ከሶርያ የሚገለጠው ለአርባ ቀን ብቻ በዓለም የሚሰለጥነው አደጃል መታየት ፣
- የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ከዚያም ሚስት ማግባቱ ልጆች መውለዱ ሰውን ሁሉ ወደ እስልምና መጥራቱና ለአርባ ዓመታት ምድርን በሰላም ገዝቶ አርባው አመት ከተፈፀመ

በኋላ እንደ ሞተና ከነብዩ መሐመድ ጐን እንደሚቀበር ይታመናል።

- ፀሐይ ከምዕራብ መውጧቷ
- በመጨረሻው ካኢባ ሙሉ በሙሉ ይፈርስና የቁመቱን ቅጽ /ኮፒ/ ከመሰረቱ ተነስቶ ወደ ፈጣሪ መወሰዱ ናቸው። በሙስሊሞች ዘንድ ስለ ምፀአቱ ያላቸው መረዳት የተለያየ ነው በክርስቲናው እንደ ሚታየው የአንዱ ትምህርት ከሌላው እንደሚለይ ሁሉ በእስልምና ዘንድ የጌታን ዳግም መመለስ አስመልክቶ ያላቸው መረዳት የተለያየ ነው። የጌታ ኢየሱስ ዳግም ምፀአት ቅደም ተከተል በወግ አጥባቂዎችና በኦርቶዶክስና እስላም መካከል ያለው ልዩነት

1. አደጃል /ሐሰተኛው ክርስቶስ አስቀድሞ መገለጥ
2. ዒሳ ከሐሰተኛው መታየቱ ቀጥሎ ይመጣል ይላሉ።
3. ሙጃዳድ / ቀናኢ አዳሽች/
4. መሐዲ

የዛሬው ዘመን ወግ አጥባቂዎች

1. አልመሐዲ
2. መጃዲድ
3. አደጃል
4. ዒሳ /ክርስቶስ/

3. ሰይጣን /ጂኒ /

ሰይጣን በእስልምና እምነት የክፉ ነገር ሁሉ ምንጭ እንደሆነ ይታመናል። ወደ ጥፋት የመጣው በክፋቱ ነው። አላህ ለመላእክት ለፈጠርሁት ሰው ስገዱ ባለ ጊዜ ባለመታዘዙ ምክንያት ተጣለ። ለመላእክትም ለአዳም ስገዱ ባልናቸው ጊዜ አስታውሱ ወዲያውም ስገዱ ኢብሊስ ብቻ ሲቀር ከጭቃ ለፈጠርከው ሰው እሰግዳለሁ? አለ

ንገረኝ ይህ በኔ ላይ ያበለጥከው ነውን እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ ብታቆየኝ ዘሮቹን ጥቂት ሲቀሩ ወደ ስህተት በእርግጥ አስገባቸዋለሁ አለ ::

አላህም አለው :- ኺድ ከነሱም የተከተለህ ገሀነም የተሟላች ቅጣት ስትኾን ፍዳችሁ ናት::ከነሱም የቻልከውን ሰው በድምፅህ አታል በነሱም ላይ በፈረሰኞችህ በእግረኞችህም ኾነህ ለልብ በገንዘቦቻቸውም በልጆቻቸውም ተጋራቸው ተስፋ ቃልም ግባላቸው ሰይጣንም ማታለልን እንጂ ተስፋ ቃልን አይገባላቸውም:: ሱራ 17፥61-64 ሱራ2፣36 ሱራ15፥26-43 አታላይ ነው ሱራ 8፥48 ተከታዮቹን የሚነቅፍ የማይደግፍ ነው ሱራ 16፥98-99 የፈጣሪን ሀሳብ ይቃወማል ሱራ 7፥200-201 ከሰይጣንም /በኩል/ ጉትጎታ ቢያገኝህ በአላህ ተጠበቅ እርሱ ሰሚው አዋቂው ነውና :: እነዚያ የተጠነቀቁት ከሰይጣን የኾነ ዘዋራ በነካቸው ጊዜ ጌታቸውን ይገነዘባሉ ወዲያው እነርሱ ተመልካቾች ይሆናሉ::

## <u>*በመንግሥተ ሰማይና በገሀነም እሳት ያላቸው እምነት*</u>

እስልምና መንግስተ ሰማያት ሆነ ገሀነም እሳትን ለሰው አእምሮ ሊገባ በሚችል ሥእላዊ ቋንቋ ይገልፀዋል:: በዚህ ዓለም ጉዞአቸውን በታማኝነትና በንፅህና ለጨረሱ ለእነርሱ ልዩ ቦታ ይህ ቀረሽ የማይባል ጥሩ ሀብትና እንዲሁም በአስፈላጊ ነገሮች የተሞላችው መንግስተ ሰማያት ሲጠብቃቸው በዚያው አንፃር የዚህ ዓለም ኑሮአቸውን በአመፅና ባለመታዘዝ በክህደት ለተሞሉት ደግሞ ገሀነም አስፈሪ አስቃቂና በቃላት መግለፅ የማይቻል የተዋረደ ሥፍራ ነው ብለው ያስተምራሉ::

መንግስተ ሰማይ የሚለው ቃል በተለያዩ ምክንያቶች ከሰዎች አንደበት ሲወጣ እንመለከታለን በጣም ጥሩ የሆነ ከተማ ወይም መናፈሻ ሰዎች ሲመለከቱ መንግስተ

ሰማይ ይመስላል ብለው በማወዳደር አድናቆታቸውን ይገልፃሉ።

ቁርአን መንግስተ ሰማያትን የገለፀበት መንገድ አብዛኛው ሀሳብ ከመፅሀፍ ቅዱስ ጋር ተመሳሳይ ነው ይህን አስመልክቶ ጥቂት የቁርአን ጥቅሶችን እንመልከት።

ከዚችው የሚበልጥ ልንገራችሁን? በላቸው(እርሱም) ለነዚያ ለተጠነቀቁት ሰዎች በጌታቸው ዘንድ በሥራቸው ወንዞች የሚፈስባቸው ገነቶች በውስጡ ሁል ጊዜ ነዋሪዎች ሲሆኑ ንፁህ የተደረጉ ሚስቶችም ከዓላህም የሆነ ውዴታ አላቸው አላህም ባሪያዎቹን ተመልካች ነው ሱራ3፥15 አላህ ምእመናንንና ምእመናትን ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲኾኑ በመኖሪያ ገነቶችም ውስጥ መልካም መኖሪናያ ቤቶችን ቃል ገብቶላቸዋል ከአላህም የኾነ ውዴታ ከሁሉ የበለጠ ነው። ይህ እርሱ ታላቅ እድል ነው። ሱራ9፥72

ዒሳ ካለው ጋር ተመሳሳይነት አለው ልባችሁ አይታወክ በእግዚአብሔር እመኑ በእኔም ደግሞ እመኑ በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር ሥፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ሄጀም ሥፍራ ባዘጋጅላችሁ እኔ ባለሁበት እናንተም እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።
ዮሐ. 14፥1-3

ከነዚያ ከኃጢአት የተጠነቀቁት በአትክልቶችና በምንጮች ውስጥ ናቸው። ፀጥተኞች ሆናችሁ ግቡባት ይባላሉ። ባልጋዎችም ላይ ፊት ለፊት የመቀጣጫ ወንድማማቾች ኾነው በደረታቸው ውስጥ ከቂም ያለውን ሁሉ እናመስግናለን። በርሷም ውስጥ ድካም አይነካቸውም እነርሱም ከርሷ የሚወጡ አይደሉም።ሱራ15፥45-48

ለነርሱስ ባሮቼ ሆይ ዛሬ ቀን በናንተ ፍርሀት የላባቸውም እናንተም የምታዝኑ አይደላችሁም ታዛገሮች የነበሩ ባሮች ገነት ግቡ

እናንተም ሚስቶቻችሁም ትደሰታላችሁ ትከበሩም አላችሁ /ይባላሉ/:: ከወርቅ የኾኑ ሰፋፊ ዝርግ ሳሕኖችና ኩባያዎች በነርሱ ላይ ይዞራሉ በርሷም ውስጥ ነፍሶች የሚከጅሉት ዓይኖችም የሚደሰቱበት ሁሉ አለ እናንተ በውስጧ ዘላለም ዘውታሪዎች ናችሁ:: ይህችም ያቺ ትሠሩት በነበራችሁት ዋጋ የተሰጣችኋት ገነት ናት:: ለእናንተ ብዙ ፍራፍሬዎች አሏችሁ ከርሷም ትበላላችሁ:: ሱራ 43፥68-73

ሸሪያ :- የቃሉ ትርጉም ወደ መታዘዝ የሚያደርስ የሕይወት መንገድ ማለት ነው:: ሸሪያ ከፈጣሪ የተሰጠ የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎት ማርኪያ ገደብ የለሽ ፍላጎት መለጎሚያ የቅድስና የዕቅድ መንገድ ማስተማሪያ እንዲሆን ከፈጣሪ የተላከ መመሪያ ነው ይላሉ::

ይህ መመሪያ በውስጡ ያልያዘውና የማይለው ነገር የለም ሰው ይህ መመሪያ ቢታዘዝ እርጭ ያለ ህይወት እንዲሁም ፈጣሪን የሚጠብቅበትን በሙሉ አሟልቶ ይኖራል ይላሉ በአጠቃላይ የእስላሙ አለም የህይወት ፍልስፍና እንዲሁም የእውነት ሁሉ እንብርት ሸሪያ ነው::

1ኛ ከሰማይ የወረደው መፅሐፍ ነው

2ኛ ሐዲስና ሱና የነብዩ መመሪያ /አባባል/ የኑሮ ልማድ

3ኛ ኢጃማ የእስልምና ምሁራን ስምምነት

4ኛ ቂያ በማወዳደርና በማነፃፀር የሚሰጥ የመግባቢያ ሀሳብ

የእስልምና እና የክርስትና ትልቁ ልዩነት የእስልምና እምነት የበዛው ትኩረት በሕግ/ሸሪያ/ የክርስትና ትኩረቱ በወንጌል ላይ ነው ይህ ማለት ደግሞ በእስልምና የሰው ደህንነት ሚወሰነው ልፋትና ጥረት ላይ ብቻ ነው:: በክርስትና ግን ደህንነት የእግዚአብሔር የቸርነት ሥጦታ ላይ ነው::እስልምና ሰው ደህንነት እንዲያገኝ ምን ማድረግ እንዳለበት ሲያመራ ክርስትና ግን እግዚአብሔር ለሰው ያከናወነው የማዳን ስራ ያበስራል እስልምና እኛ ምን መስራት

እንዳለብን ሲያስገነዝበን ክርስትና ግን እግዚአብሔር ምን እንደሰራልን ያስገነዝበናል እስልምና ሕጉን ታዘዝ የሚል የጥሪ ጩኸት ሲያሰማ ወንጌሉ ግን እግዚአብሔር ሰውን ለማፅደቅ የፈጸመውን የማዳን ሥራ ያውጃል::

ዑማ፡- የእስልምና ማሕበረሰብ በአረብኛው አጠራር ዑማ ተብሎ ይጠራል ዑማ የፈጣሪ ወኪል ሕብረተሰብ ነው::

ለሰዎች ከተገለፁት ህዝብ ሁሉ በላጭ ሆናችሁ በፅድቅ ነገር ታዛላችሁ ከመጥፎም ነገር ትከለክላላችሁ በአላህም /አንድነት/ ታምናላችሁ የመጽሐፉም ሰዎች ባመኑ ኑሮ ለነርሱ የተሻለ በኾነ ነበር:: ከነርሱ አማኞች አሉ አብዛኞቹ ግን አመጸኞች ናቸው:: ሱራ 3፥110

ይህ ህብረተሰብ የተመሰረተው መሐመድ ወደ መዲና በስደት በሄደ ጊዜ ነው :: በጊዜው ከመካ የተሰደዱት ሙሃጅሪም እና የመሐመድን እርዳታ ፈልገው የጠሩት ረዳቶቹ አንሷር ይህን ማኅበረሰብ መሰረቱ::

በጥቂቱ የተጀመረው ይህ ማኅበረሰብ ወደ ዓለም አቀፍ ቤተሰብ ተለውጧል:: መካ የዚህ ቤተሰብ መገኛ ነች ይላሉ::

የዚህ ማኅበረሰብ መመሪያው ሸሪያ ነው:: መሐመድ በመካ የነበረበትን አሰቃቂ መከራ በመሸሽ በመዲና ተቀባይነትን አግኝቶ ኋላም በኃይለኝነቱና በአሸናፊነቱ ይህን ቤተሰብ መሰረተ::

የመስቀሉ መንገድ ከዚህ የተለየ ነው:: ኢየሱስ የነበረውን መብትና ተቀባይነት ገና ከጅማሬው የተወ በመሆኑ እንዲህ ዓይነቱ ግብዣ ቢቀርቡለትም ፈቅዶ በመተው በፊቱ ያፈጠጠውን መከራ ተጋፍጦ ወደ መከራ መሀል በመግባት በውርደቱ ክብርን፣ በጭንቀቱ ሰላም በሞቱ ሕይወትን አግኝተናል:: ስለዚህ ኢየሱስ የፖለቲካ ሀይል በማዋቀር ሳይሆን መግለጫ በሌለው የፍቅር የመስዋዕትነት ሞቱ የእግዚአብሔር መንግሥት በሰው ታሪክ ውስጥ ገለጠ::

የእግዚአብሔር መንግሥት የምትሰፋው በፀጥታ ነው። ምክንያም ባህሪዋ በዳቦ ውስጥ እንዳለች ጥቂት እርሾ በጨለማ እንደሚበራ ጥቂት ብርሀን በምግብ ውስጥ እንዳለ ጨው ናት። በሰው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ አላት።

የአሁኗ ቤተክርስቲያን ከብዙ ጉድለቷ ጋር የእግዚአብሔር መንግሥት ውክልና ተሰጥቶአታል። ሰዎች በልብ ንጽህና እና በደስተኝነት ከፈጣሪና ከመሰል ወገኖቻቸው ጋር ቀና ኅብረት በፈጠሩበት ሥፍራ ሁሉ መንግስቱ አለ ከየትኛውም ድርጅታዊ ሥርዓት ምድራዊ መንግስት ጋር የእግዚአብሔር መንግሥት አይያያዝም።

የክርስትና ታሪክ የሚጀምረው ከመከራና ከሞት ነው። የእስልምና ታሪክና ካላንደር የሚጀምረው ከአሸናፊነትና ተድላድሎ ከተቋቋመ አንድ ድርጊት ነው።